

ቅዱስ ፓትርያርኩ ጥንታዊና ታሪካዊ የሆነውን በጎንደር ከተማ የአጼ ፋሲልን ግንብ በጎበኙበት ወቅት ።

# ትንሣኤ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት በወረታ ሕጻናት ማሳደጊያ ሕጻናትን በአባታዊ ፍቅር ሲያጽናኑ ።

"ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር ፶፫ የካቲት ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

‘‘ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጕምር እንዲተረ ጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ‘‘ትንሣኤ’’ ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም አዘጋጅ ራደ አስረስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ጾም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ. ቤ. ክርስቲያን | ፪ |
| ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት | ፫ |
| ዜና ሊቃውንት | ፬ |
| ጾም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን | ፭ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፮ |
| በኢሉባቦር ክ ሀገር የጋምቤላ ብሔረሰቦች | ፯ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲፩ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፲፫ |
| ሊቀ ማእምራን ሐዋዝ | ፲፬ |
| ጉቦ የዓይናማዎችን ዐይን ያሳውራል | ፳፫ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

በመጀመሪያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። ከሰላምታዬ ቀጥሎ ያልገቡኝን ነገሮች እንድታስረዱኝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትሕትና አቀርባለሁ።

1ኛ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ 14፡ 34 ላይ « ሴቶች በማሕበር መካከል ዝም ይበሉ አይናገሩ » ይላል እንዲህ ሲል ምን ማለቱ ነው ?

2ኛ በማርቆስ ወንጌል 9፡ 1 ላይ ያለው ቃል ስላልገባኝ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ አስረዱኝ

3ኛ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 4 ላይ « ዮሐንስ ልብሱ የግመል ጠጉር ነበረ ምግቡም የበረሃ አንበጣ ነበረ ይላል አንበጣ የተባለው ምንድን ነው?

4ኛ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ያስተማረው የመጨረሻ ነቢይ ማን ይባላል ?

5ኛ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 19 ቁጥር 24 « ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል » ይላልና ምን ማለቱ ነው ?

ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ
ከመንበረ ሕይወት መድኃኔ ዓለም
የፖስታ ሣ. ቁ . 44
አቃቂ በሰቃ
ሸዋ

ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ ስለ ጥያቄዎችህ እናመሰግናለን ።

1ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሴቶች በማሕበር መካከል አይናገሩ » ማለቱ፡ እርሱ በነበረበት ዘመን ሴቶች በአደባባይ እንዳይናገሩ የሕብረተሰቡ ልማድ ነበር ።

ነገር ግን የክርስትና ሃይማኖት « ሴትና ወንድ በክርስቶስ እኩል ናቸው » ስለሚል በዚያ ጊዜ የነበሩ ክርስቲያን ሴቶች ቀደም ሲል የነበረውን ሥርዐት በክርስትና ምክንያት እንዳይቃወሙ ጳውሎስ አስተምሮአል ። ቅዱስ ጳውሎስ የኅብረተ ሰቡን ጊዜያዊ ሥርዐት ቢቃወም ኖሮ ወንጌልን አስፋፍቶ ለማስተማር ባልቻለም ነበር ። ከእርሱ በኋላ ግን በክርስቶስ የተሰጠው ነፃነትና እኩልነት በወንዶችና በሴቶች ዘንድ እየተስተዋለ ሲሄድ ሴቶች እንደወንዶች በማሕበር እንዲናገሩና እንዲያስተምሩ ተደረገ ።

እርግጥ ያንጊዜም ቢሆን ሴቶች በማሕበር እንዳይናገሩ ሥርዐት የነበራቸው የቆሮንቶስና የኤፌሶን ሰዎች ብቻ እንደነበሩ ይገመታል ። ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ ሥርዐታቸውን ሳይቃወም በጥበብ አስተምሮአል ።

2. በማርቆስ 9 ፡ ላይ « እዚህ ከቆሙት ሰዎች መካከል በኃይል ሲመጣ የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አሉ » ይላል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተናገረ በደብረ ታቦር ምሥጢረ መንግሥቱን ከመግለጡ በፊት ነው ። ስለዚህም በደብረ ታቦር ብርሃን መለኮቱን ሲገልጥ እስኪያዩ ድረስ ሐዋርያት የማይሞቱ መሆናቸውን ያመለክታል ። በሌላም በኩል ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ እስኪያዩት ድረስ ደቀመዛሙርቱ አይሞቱም ማለት ነው ። በተጨማሪም ጌታችን በተናገረው ትንቢት መሠረት በ70 ዘመን ኢየሩሳሌም በጥጦስ ኃይል ስትጠፋ እስኪያይ ድረስ ከሐዋርያት መካከል ወንጌላዊው ዮሐንስ የማይሞት መሆኑን ያሳያል ። ሌሎች ሐዋርያት ሁሉ ከኢየሩሳሌም ጥፋት በፊት ሲሞቱ ዮሐንስ ብቻ እስከ ፺ ዓመት ቆይቷልና።

3. የመጥምቁ ዮሐንስ ልብሱ ወንጌሉ እንደሚለው ከግመል ጠጉር የተሠራ ማቅ ወይም ባና ነበር ። ይህንም አይነት ልብስ ነቢያት ሁሉ ይለብሱ ነበር ። የኤልያስም ልብስ የዚሁ አይነት ነበር። ዘካ 13፡ 4። 2 ነገ 1፡8 ዮሐንስም ዳግማዊ ኤልያስ ነበርና ከግመል ጠጉር የተሠራ ማቅ ይለብስ ነበር ። የሀገራችን ሊቃውንት ግን የዮሐንስ ልብስ ገመሌ ከሚባል ዕንጨት ልጥ የተሠራ ነበር ይላሉ። ምግቡም አንበጣ ነበር የሚለው ትክክለኛ ነው በዚያ ጊዜ በይሁዳ አውራጃ አንበጣ ይበላ ነበር ።ዛሬም በሰሜናዊ ምሥራቅ አፍሪቃና በመካከለኛው አፍሪቃ ሕዝቦች ዘንድ አንበጣ ይበላል በብሉይ ኪዳንም ሙሴ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትን ለይቶ ሲናገር እነዚህን ትበላላችሁ ዙዋሪ አንበጣ ኩብኩባ በየዘመዱ ደጎብያ በየ ዘመዱ ፡ ሣር ዘላይ አንበጣ በየዘመዱ » ዘሌዋ. 11 ፡ 22 ።

4 . ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ያስተማረው የመጨረሻው ነቢይ መጥምቁ ዮሐንስ ነው።

5. በማቴዎስ 19፡24 « ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል » የሚለው ዐረፍተ ነገር በዚሁ ምዕራፍ ከቁ. 16 - 22 የተጠቀሰውን ባለጠጋና ሌሎች ንፉጎች ባለጠጎችን ብቻ የሚመለከት እንጂ ባለጠጎችን ሁሉ የሚመለከት አይመስልም ምክንያቱም ንብረታቸውን በሙሉ ለድሆች ሰጥተው የእግዚአብሔርን መንግሥት የወረሱ ብዙ ባለጠጎች አሉና። «ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል» ማለትም ለጊዜው የማይሆን ነገርን ሁሉ የሚመለከት ነው ። ይህንም የመሰለ በአይሁድ ዘንድ ሌላ የንግግር ዘዬ ነበር። ለምሳሌ በጠባዩ ሊታገሡት የማይችሉትን ሰው «አንተን ከመሸከም ዝሆን መሸከም ይቀላል» ይሉ ነበር ።ይህም ዘዬ ምንም እንኳ ሊደረግ ቢችልም ለጊዜው አስቸጋሪ መሆኑን ያመለክታል ። ነገር ግን በጌታ ዘንድ የማይቻል ነገር የለምና ግመል በመርፌ ቀዳዳ ሊያልፍ ይችላል ። ይህም በሐዋርያው ታዴዎስ ጊዜ ታይቷል።



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ጾም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በዓለም ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ለተከታዮቻቸው የጾምን ጠቃሚነት ያስተምራሉ ። የየራሳቸው
ም የሆነ ሥርዓተ ጾም አላቸው ፤ አፈጻጸሙ ግን እንደ እየሀገሩ ባሕልና ልማድ ይለያያል ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያትና ከሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት
የተቀበለቻቸውና ለተከታዮችዋ የምታስተምራቸው ሰባት አጽዋማት አሉ ፡ -
እነርሱም ፡ - ሀ ዐቢይ ጾም ለ ጾመ ረቡዕ ወዓርብ ሐ ጾመ ነነዌ መ የልደትና የጥምቀት ገሃድ ሠ ጾመ ነቢ
ያት የኅዳር ጾም ረ ጾመ ሐዋርያት የሰኔ ጾም ሰ ጾመ ፍልሰታ ናቸው ። በነዚህ አጽዋማት ወቅት እስከ ሰዓት
ድረስ ምንም አይነት ምግብ መቅ መስ አይፈቅድም ቅዳሴም የሚቀድሰውና ሥርዓተ ቁርባን የሚፈጸመው በሰዓ
ት ነው ። ከሰዓት በኋላም ጥሉላት አይበላም ።

በመሠረቱ ጾም ለተወሰኑ ቀናት ከተወሰኑ የምግብ አይነቶች መከልከል ነው ። እንዲሁም በዐይን አይቶ
ከመጎምጀት በአንደበት ክፉ ተናግሮ ሌላውን ከማስቀየም በጆሮም ሰምቶ ከመሳት መከልከል እንደሚገባ የኢ
ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ። ከዚህም ጋር ጾም ፤ ጸሎትና ምጽዋት በአንድነት
የሚሠሩ ምግባራት መሆናቸውን በመገንዘብ ምጽዋት የገንዘብ ግብር ዓሥራት ሲሆን ጾም ግን የሥጋ ግብር
እንደሆነ ትሰብካለች ።

በጾም ጊዜ ከተወሰነ የምግብ አይነት መከልከል ወይም መለየት እንደሚገባ ሁሉ ከሥጋዊ ፈቃድ መከ
ልከልም ከጾም አንዱ ክፍል ነው ስለሆነም ባልና ሚስት በክፍል ሳይሆን በአልጋ ተለያይተው ይጾማሉ ። የጾም
ወቅት መዋዕለ ኀዘን ስለሆነ ጾዋሚዎች ሁሉ ከማንኛውም ተድላና ደስታ ይከለከላሉ ።
በጾም ጊዜ ተድላ ደስታ ማድረግ የማይገባ ከመሆኑ የተነሣ ጋብቻና የመሳሰሉት ሁሉ ተከልክለዋል ።
በተለይ በዓቢይ ጾም በጥምቀተ ሕፃናትና በበዓለ ስማዕታት ምክንያት ጠላ ጠምቆ ዳስ ሠርቶ ሰው ጠርቶ መጋ
በዝ እንደማይገባ በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ 15 ተወስኖአል ።

በገዳም የሚኖሩ ጽሙ ዳን መነኮሳት ደግሞ ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ ይጾማሉ ይኸውም 1ኛ ጾመ ሠግር የአ
ክፍሎት ጾም ሲሆን ሁለተኛ በ24 ሰዓት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ በመመገብ ነው ። ጾመ ሠግር እሁድ በልቶ ማክ
ሰኞ ማክሰኞ በልቶ ፤ ሐሙስ ሐሙስ በልቶ ቅዳሜ በመብላት የሚጾሙ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ከላመ ከጣመ ምግ
ብ ተከልክለው ጭብጥ ሽንብራ ጥሬ ብቻ እየቀመሱ ይጾማሉ ። በዚህ ዓይነት የሚጾሙ አጽዋማት አብዛኛውን
ጊዜ ዐቢይ ጾም ሕማማትና ጾመ ፍልሰታ ሲሆኑ ጾዋሚ ዎቹም ጽሙ ዳን መነኮሳት ናቸው ።
በገዳመ ዋልድባ የሚኖሩ መነኮሳት በቀሩት አጽዋማት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ለቁመተ ሥጋ ያህል የሚ
መገቡ ሲሆን በፍልሰታ በዓቢይ ጾምና በሕማማት በሳምንቱ ውስጥ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ብቻ እየተመገቡ
ያከፍላሉ ይጾማሉ ። ውሃ በመቅዳት ፤ እንጨት በመልቀም ፤ ቋርፍ በመቀቀልና ኑግ በመውቀጥ አበው መነኮሳት
ን የሚረዱ አርድእት ግን በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እየተመገቡ ይሠራሉ ፤ አርድእቱ የአክፍሎት ጾም እንዳይጾሙና
በቀን አንድ ጊዜ እንዲመገቡ የሚፈቀደው ውሃ ቀድተው እንጨት ለቅመው ቋርፍ ቀቅለው አበው መነኮሳትን
መርዳት እንዲችሉ ነው ። በጾምና በጸሎት የተወሰኑ አበው መነኮሳት ግን በተለይ በስሙነ ሕማማት የሆሣዕና
እሁድና የጸሎተ ሐሙስ ብቻ ጥቂት ጥቂት እየቀመሱ እስከ ትንሣኤ ዕለት ድረስ ያከፍላሉ ። በማለት መምህር
ገ ሥላሴ ገብሩ ያስረዳሉ ።

ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ሰባት አጽዋማት ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ክርስቲያኖች
ሁሉ መጾም እንደሚገባቸው በፍትሕ መንፈሳዊ ተገልጦአል ። ግን አንድ ክርስቲያን ቢታመምና የበሽታው
ሁኔታ የጾም ምግብ ብቻ ለመመገብ የማያስችለው ቢሆን በሐኪም የታዘዘለትን እንዲመገብ ቤተ ክርስቲ
ያን ትፈቅዳለች ። እንዲሁም ለወላዶችና ለሠራተኞች የሥራው ክብደትና የሁኔታውን አስፈላጊነት እየገመገመ
ች መፍቀድ ትችላለች ። ምክንያቱም የቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ሥርዓተ
ጾምንና የመሳሰለውን ሁሉ ከሠሩ በኋላ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በመንፈስ ቅዱስ
መሪነት እንደሚሠሩ አምነው የኋላ ሊቃውንት የቀለለውን ማክበድ የከበደውንማቅለል እንደሚችሉ ወስነዋል ።



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ጎንደርንና ጎጃምንጎበኙ

ጐንደር ፡ - ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክ ይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር በጎንደርና ጎጃም ክፍላተ ሀገር ጥንታውያን ሥፍራዎችንና ገዳማትን እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመጀመሪያ የጎንደርን ግፍለ ሀገር ለመጎብኘት ጥቅምት 28 ቀን 1974 ዓ ም. ከጥዋቱ 4 ሰዓት አዘዞ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ ብፁዕ አቡነ መርቆሪዎስ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ፤ ጓድ ዘመነ ካሳ የጎንደር ክፍለ ሀገር ረ ዋና አስተዳዳሪ የመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ተጠሪዎች የጎንደር ከተማ የአርባ አራቱ አድባራት አስተዳዳሪዎች ፡ ሊቃውንት ካህናት ፤ የከተማው ሕዝብ እጅግ ደማ



በቅዱስነታቸው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ሊቃውንቱ ሲዘምሩ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አዘዞ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና የክ ሀገሩ ረ ዋና አስተዳዳሪ አቀባበል ሲያደርጉላቸው ።

ባና በዕልልታ ፤ ታሪካዊ የሆነ አቀባበል አድርጎላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን የሆኑትን ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ፡ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና ሌሎችንም የልዑካኑ አባላትን አስከትለው ጎንደር ከተማ መስቀል አደባባይ ከተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ እንደደረሱ ሊቃውንቱ ለአቀባበሉ የተዘጋጀውን ግሥ ለ 20 ደቂቃ አሸብሸበ ቅ የሆነ አቀባበል አድርጎላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከአውሮፕላን ሲወርዱ ሁለት ሕጻናት ዕቅፍ አበባ አበርክተው ላቸዋል ።


ከአዞዞ እስከ ጎንደር ከተማ ድረስ ተሰልፎ በየመንገዱ ዳር ይጠባበቅ የነበረው ሕዝብና ልብስ ተክህኖ የለበሱ ካህናት በዝማሬ ፤ ሕዝቡ በጭብጨ



www.ethiopianorthodox.org

ውታል ።

ቅዱስነታቸው በአቀባበሉ ሥነ ሥር ዓት ላይ ባሰሙት ቃለ ቡራኬ « ሀገረ እግዚአብሔር ጎንደር የታሪክና የእው ቀት ምንጭ የሆነች ታሪካዊት ቦታ በመ ሆኑዋ በውስጧ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ሚታዩት አጉልና ጎጂ ባህሎች መታረ ም እንዳለባቸው ቅዱስ አባታችን በሰ ጡት አባታዊ ቃለ በረከት ሲገልጹ « በ ዚች የክርስቲያን ሀገር በሆነችው ጎን ደር በመንፈሳዊ ጥርቦችዋ የምንመካባ ት ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ከጥንት



ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ቅዱስነታቸውን እንኳን ደኅና መጡ በማለት ንግግር ሲያደርጉ ።



ቅዱስነታቸው ሊግሊሞ አፋፍ ላይ ሆነው አካባቢውን ሲመለከቱ ።

ጥንታውያን ቅርሶችና ታሪካውያን ስ ፍራዎች ለመጎብኘት ስንመጣ የተደረ ገልን አቀባበል ደስ የሚያሰኝ ነው ብለ ዋል ።

እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎች ስለ ሲያያዝ የመጣና ጠቃሚ ያልሆነ በክር ስትና ሃይማኖትም የማይደገፍ ጎጂ ባህ ል በመታየቱ ቅር የሚያሰኝ ነው ።

እንዲህ ዓይነቱ ባህል በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዓለም የማይጠቅም በመሆኑ ከአሁን ጀምሮ ሊቀር ይገባል ይኸውም 1ኛ ሰው በሞተ ጊዜ በመሪር ኀዘን ፊት መቧጠጥ ፣ ፀጉር መንጨት፣ ደረት መድቃት ፣ የመሳሰለው ሁሉ በት ንሣኤ ሙታን የማያምኑ ፣ ተስፋ የቆረ ጡ ሰዎች የሚያደርጉት እንጂ ክርስቲ ያኖች ሊፈጽሙት የማይገባ ተግባር በ መሆኑ ከአሁን ጀምሮ መቅረት አለበት። ማንም ሰው ሲሞት ፣ ሁሉም በተራው ይሞታል የሞተን ሰው ማስመለስ የ ማይችል መሪር ኀዘን ማዘን ግን ቋሚ ውን ለበሽታ የሚያጋልጥ ሰውነትን የ ሚጎዳ በመሆኑ ከዛሬ ጀምሮ እንዲህ ዓ ይነቱ ጎጂ ባህል ፈጽሞ መቅረት አለበ ት ካሉ በኋላ እንዲሁም በአንዳንድ ቀበ ሌዎች ሴቶች ልጆችን ለአቅመ ሄዋን ሳይደርሱ በሕፃንነታቸው መዳር የሚ ያስከትለውን ጉዳት በመዘርዘር ቅዱስ ነታቸው ባሰሙት ንግግር « ሕፃናት ኃ ላፊነትን መሸከም የማይችሉ መሆናቸ ውን ወላጆቻቸው እያወቁ በሕፃንነታ ቸው መዳራቸው የወላጅነት ኃላፊነታ ቸውን ዘንግተው ከጉዳት ላይ እንደጣ ሉዋቸው ባለማወቅ ካልሆነ በቀር ለጥ ቅም አይደለም ። ሕፃናት በቤተሰቦቻቸ ው ኃላፊነትና እንክብካቤ አድገው ኃላ ፊነት ሲሰማቸው ክፉውንና ደጉን ለይ ተው ሲያውቁ በመረጡት ሀሳብ መመ ራት ሲገባ ቸው ገና በሕጻንነታቸው ተድ ረው ኃላፊነቱን መሸከም ሲያቅታቸው ይኮበልላሉ በከባድ ችግር ላይ ም ይወ ድቃሉ ። ይህ እንግዲህ ለፍች ዋናው ም ክንያት በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸው ክፉውንና ደጉን ተረድተው በፈቃዳቸ ው መመራት እስከሚችሉ ድረስ በኃላ ፊነት ተንከባክበው ማሳደግ አለባቸው እንጂ ሕፃናቱን እያነቁ መዳር ተገቢ ባለ መሆኑ ከአሁን ጀምሮ መቅረት አለበት ብለዋል ። ከዚያ ቀደም ብሎ ግን ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የጎንደር ሀገረ ስብከ ት ሊቀ ጳጳስ እንኳን ደኅና መጡ በማለ ት ባደረጉት ንግግር ቅዱስነታቸው ክፍላተ ሀገርን እየተዘዋወሩ በመ ጎብኘት በተለይም ብዙ ገዳማትና አድ ባራት ያሉባት አራቱ ጉባዔያት የሚነ ገሩባት የድጓ የዝማሬ መዋስዕት የላይ ቤት የታች ቤት አቋቋም ከነባህሉ የሚ ነገሩባትን ጎንደርን በመጎብኘታቸው የተሰማ ቸውን ደስታ ገልጠዋል ።


እንዲሁም ጓድ ዘመነ ካሣ የጎንደር ክፍለ ሀገር ሪ ዋና አስተዳዳሪ ቅዱስነ ታቸውን እንኳን ደህና መ ጡ በማለት ባሰሙት ንግግር ቤተ ክርስቲያን ማይ ምነትን በመዋጋት ፣የደን ሀብትን በመ ንከባከብ ፣ አጉልና አስከፊ ባህሎች እ ንዲወገዱ እስካሁን ድረስ ያደረገችውን ጥረት አድንቀው ወደፊትም በዚሁ ዓላ ማዋ ተሰልፋ መንግሥትን እንደምትረዳ ተስፋ አለኝ ካሉ በኋላ በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ክፍለ ሀገሩን እየጎበኙ በሚቆዩበት ጊዜ ለክፍለ ሀገሩ ዕድገትና ልማት ሰፊ ምክር እንደሚለግሱ እናም ናለን ብለዋል ።



ቅዱስነታቸው በመሠራት ላይ ያለውን የአደባባይ ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን በጎበኙበት ወቅት ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ገለጻ ሲያደርጉ ።

ከዚህ በኋላ ሊቃውንቱ በየተራ ብዙ ቅኔዎችን አበርክተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ታሪካዊውን የአፄ ፋሲልን ግንብ በጎበኙበት ወቅት ።

ለስድስት ቀናት ያህል በከተማው እየ ተዘዋወሩ የልማት ቦታዎችን፣ አድባራ ትን ገዳማትን ጎብኝተዋል ።

ቅዱስነታቸው ጉብኝት ባደረጉባቸው ቦታዎች ሁሉ ደማቅ አቀባበል ተደርጎ ላቸዋል ።እንዲሁም የሰሜንና የወገራ አውራጃዎችን እየተዘዋወሩ የጎበኙ ሲ ሆን በሰሜን ርዕሰ ከተማ ደባርቅ በወገ ራ ርዕሰ ከተማ ዳባት የየአውራጃው ባለሥልጣኖች የከተማው ሕዝብና ካህናቱ እጅግ ደማቅ የሆነ አቀባበል አ ድርገውላቸዋል ።

ወደ ገጽ ፲፫ የዞረ





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## ሐዲስ ተክሌ (አቡነ ዮሐንስ)

በሊቅነታቸው የታወቁት ሐዲስ ተ ሌ ተጉለት እነዋሪ በተባለው ቦታ ከአ ለቃ ተአምራት በ1875 ዓ.ም መጋቢት 12 ቀን ተወለዱ ።



ሐዲስ ተክሌ ( አቡነ ዮሐንስ )

የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ና በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተማሩ ቀጥሎም ወደ ጎንደር ሔደው በቤተ ልሔም ቁም ዜማ እንዲሁም በጎንደር ከተማ አቋቋም በሚገባ ተምረው ካ ጠቁ በኋላ ወደዋድላ ተዛውረው ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው ለመምህርነት ተመረቁ ።

በጎንደር ከታወቁት ሊቅ ከመምህር ተክለ ማርያም ትርጓሜ ሐዲሳትን በሙሉ ከአለቃ ዘዮሐንስ ፍትሐ ነገሥትን ተምረው በወቱ የሐዲሳቱንም ትርጓሜ እንደገና ከለሱ ።

ወደ ደብረ ታቦርም ተጉዘው ከአለቃ ተሰፋ ዘንድ የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ አጠኑ ፤ ሊቁ ሐዲስ ተክሌ በትምህርት ከጉባኤ የወረሱት ትርጓሜ ሐዲሳት በሊቃውንት ዘንድ የታወቀውንና ታላቁ ሊቅ መምህር ኤስድሮስ በደሴ ተ ጣና ያቃኑትን የታች ቤት ትርጓሜ ስለሆነ የሐዲስ ትርጓሜና ምርምር ሙያቸው ከተፈጥሮ ብልህነታቸው ጋር ተ ጣምሮ ሐዲስ ተክሌ ሊያሰኛቸው ቻለ።

በመሆኑም በዚያው በጎንደር የሐዲሳትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ጉባ ኤ ዘርግተው ያስተምሩ ጀመር ቀጥሎም ወደ ማኅበረ ሥላሴ ሄደው መነኮሱ ። ከዚህ በኋላ የጎንደር ልደታን አስተዳዳሪ ነት ተሾሙና ጉባኤያቸውን ለማስፋፋት አጋጣሚ ዕድል አገኙ ራስ ጉግሣ ወሌ የተማሩትን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መንከባከብ የታወቀ ስጦታቸው ስለነበረ ሐዲስ ተክሌ ወደ ደብረ ታቦር ከተማቸው ተዛውረውና የወር ደመወዝ ተመድቦላቸው ሐዲሳት ፍትሐ ነገሥትና ቅኔ እንዲያስተምሩ አደረጉ ።

ራስ ጉግሣ የዘወትር ማዕዳቸው በሊቃውንት የተከበበ ከመሆኑም በላይ ለ ህሊናቸው የሚከብደውንና የሚረቀውን ምሥጢር መጠየቅ መረዳትና ማወቅ ስለሚፈልጉ ሐዲስ ተክሌም ለተጠየቁት ሁሉ የሚሰጡት መልስ አጥጋቢ እን ደነበር ይነገራል ።

በዚህ ጊዜ ነበር ራስ ጉግሣ ከሐዲስ ተክሌ ሌላ « ተክሌ » በሚል ስም የሚ ጠሩ የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ ሊቅ ስለነበሩ ለይቶ ለመጥራትና ለማነጋገር በመቸገራቸው ለሁለቱም ሊቃውንት «ሐዲስ ተክሌ » ብሉይ ተክሌ » በማለት ተጨማሪ የሞያ መግለጫና መለያ ቅጽል የሰጧቸው ።

ሐዲስ ተክሌ በደብረ ታቦር ሆነው ብዙ ሊቃውንትን አስተምረዋል ። ።

ከዚህ በኋላ ሊቁ በ1918 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ መጥተው የቅስና እንዲሁም የቁምስና መዓረግ ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ተቀበሉና ፈቃድ ጠይቀው በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ቅዱሳት መካናት እጅ ነሥተው ተመለሱ ። በአዲስ አበባ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ሆነው ጥቂት ጊዜ ከአስተማሩ በኋላም የአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ን ደብር መምህርነት ተሾመው ያስተምሩ ጀመር በሁለተኛውም ዓመት « መልአከ ብርሃን » ተብለው የአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴን ደብር በሹመት እንዲያስተዳድሩ ተደረገ ።

በዚህ ሹመታቸው ሦስት ዓመት ከቆዩ በኋላ ተወልደው ባደጉበት በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ተሾሙ ።

በአክሱም ሥነ ሥርዓትና ክብር በዳግማዊ ምኒልክ የተገደመው የአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን መተዳደሪያ ደምብ ከዚያ በፊት ከመንግሥት ሳይሰጠው በውዝፍ ቆይቶ ስለነበረ የደብሩን አቀዋምና አስተዳደር የሚያመለክት ደምብ ወዲያው ሊቁ እንደተሾሙ ተከታትሎ ደረሰ። ንቡረ ዕድ ተክለሃይማኖት የደብሩን አስተዳደርና እንደጊዜውም ሁኔታ የዳኘነትን ሥራ እያካሄዱ የተለመደ ጉባኤያቸውን በሰፊው ዘርግተው ያስተምሩ ጀመር የሐዲሳትና የፍትሐ ነገሥት ደቀ መዛሙርቶቻቸውንም በማስተማር ብቻ ሳይሆን በግምብና በልብስ ይንከባከቧቸው ስለነበረ በዚያን ጊዜ አዲስ ዓለም ዳግሚት ጎንደር ሆና ነበር ።

በአዲስ ዓለም ሆነው ብዙ ታላላቅ ሊቃውንትን አስተምረው ለሀገር አበርክተዋል። ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት በመጻሕፍት ትርጓሜ ዕውቀታቸው እጅግ የተመሰገኑ ቢሆንም በተለይ ከሐዲሳት በጳውሎስ ከሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት ይደነቁ ነበር ።

ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ኢትዮጵያን እስከወረረበት ጊዜ በአዲስ ዓለም የንቡረዕድነት ሥልጣን ላይ ከቆዩ በኋላ በ1929 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ገ ብር ተው እጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ጳጳስ ዘሸዋ ተብለው ተሾሙ በጠላት ዘመን አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ አቡነ ሚካኤል በኤሉባቦር ግምባራቸውን እየመከቱ

ወደ ገጽ ፰ ዞሯል

# ጾም በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት

ጾም ከተወሰኑ ምግቦች ለተወሰኑ ሰዓታት መከልከል ነው ። አንዳንድ ጊዜም ከማንኛውም የምግብ አይነት ለተወሰኑ ሰዓታት በመከልከል የሚሆን ጾም አለ ።

ጾም ከጥንት ዘመን ጀምሮ በሃይማኖታውያን ና ከሃይማኖት ውጭ በሆኑ ሕዝቦች ዘንድ የተለመደ ነበር ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ጾም በብዙ የተለያዩ ምክንያቶች የጾም እንደነበር በየአንቀጹ ተ ጽፎ ይገኛል ። ለምሳሌ ከእግዚአብሔር ጋር በራእይና በሕልም ወይም በመልአክ ለመነጋገር ለመንፈሳዊ ተልእኮ ለመዘጋጀት ከእግዚአብሔርም አንድ ነገ ር ለማግኘት የጾሙ ሰዎች ነበሩ ።

በዚህ መሠረት ሙሴ ዐሥሩ ትእዛዛትን ከመቀበሉ በፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደ ጾመ በዘጸአት 34፡ 28 ተጽፎአል ነቢዩ ኤልያስም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደ ጾመ ከእግዚአብሔር ድምጽ ሰምቶአል ። 1 ነገሥ 19 ፡ 8 ።

ማንኛውም እስራኤላዊ አንድ አስጨናቂ ነገር ሲገጥመው እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን ድር ጊት ሲፈጽም በግል መጾም የተለመደ ነበር ። ይህም የንስሐ ጾም ይባላል ። ዳዊትና አክአብ በየዘመናቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በተላለፉ ጊዜ ማቅ ለብሰው ትቢያ ነስንሰው ጾመዋል ። 2 ሳሙ 12 ፡ 16 - 23 ።።

1 ነገሥ . 21 ፡ 27 ።

በሀገር ላይ ከባድ አደጋ ጦርነትና መቅሠፍት ሲደርሱ በአዝመራ ላይ አንበጣና ተምች ሲወርዱ በሰውና በእንስሳ ላይ አባርና ቸነፈር ሲነሡ የማሕበር ጾም ይደረግ እንደነበር የሚከተሉት ጥቅሶች ያመለክታሉ ። ለምሳሌ የእስራኤል ልጆች በጊብዓ ላይ በብንያም ልጆች ድል በተመቱ ጊዜ በማኅበር ሆነው ከጡዋት እስከ ማታ ጾመዋል። መሳፍ.20፡26።የሞአብና የዓሞን ልጆች በዮሳፍጥ ላይ በኅ ይልስለተነሱ ንጉሡ ዮሳፍጥ በይሁዳ ሁሉ ጾምን አወጀ። 2 ዜና 20 ፡ 3 ። ሐማ የተባለው ጨካኝ ሰው በፋርስ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ እንዲጠፉ በመከረ ጊዜ በአስቴር ትእዛዝ አይሁድ ሁሉ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ምንም ሳይቀምሱ ጾመዋል። አስቴ . 4፡ 16 ፡ የነነዌ ሰዎችም ይህን የመሰለ ተግባር ፈጽመዋል ዮናስ. 3፡4 -10 ።

በትንቢተ ኢዮኤል አንድና ሁለት ምዕራፎች ላይ እንደተገለጠው ሀገሩን ሁሉ አንበጣ በመውረሩ የዓዋጅ ጾም ተደርጎ ነበር ።

የእስራኤል ልጆች ከምርኮ በተመለሱ ጊዜ የመከራ ቀኖችን በየዓመቱ በጾም ያስታውሱ እንደነበር ዘካርያስ ይናገራል። ዘካ 7 . 5 ። ከዚህም ጋር እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ለማስታወስ የሚያደርጉት የኑዛዜ ጾም በመጽሐፈ ነህምያ ተመዝግቦአል ። ነህም . 9፡ 1።

ሰው በሞተ ጊዜ ጾም መጾም በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነበር ። ይህም ሰውየው ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚቀበርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከሞተም በኋላ ከአንድ ቀን እስከ ሰባት ቀናት የሚጾም ነው ። 1 ሳሙ . 31 ፡ 13 ። 2 ሳሙ 1 ፡ 12። እግዚአብሔር አምላክ ለእስራኤላውያን በሰጣቸው ሥርዐተ በዓል በሰባተኛው ወር በዐሥረኛው ቀን የማስተማሪያ ቀን ነበር በዚህም ቀን የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሰውነታቸውን እንዲያስጨንቁ ታዘዝዋል ዘሌ 23 ፡ 27 - 32 ። ሰውነትን ማስጨነቅ ማለትም በጾም ነው ። ከዚህም የተነሣ ጾም ሥጋን ማስጨነቅና ማድከም ለነባቢት ነፍስም ማስገዛት ነው ተብሎ ተተርጉሞአል ።

የጾም ቀናት በብሉይ ኪዳን ለአንድ ለሶስት ለሰባትና ለአርባ ቀናት እንደ ነበሩ እላይ በተዘረዘሩት ታሪኮች መረዳት ይቻላል ነገር ግን ከአንድ ቀን በታች ከአርባ ቀናትም በላይ የሆነ የጾም ጊዜ መኖሩ በብሉይ አልተጠቀሰም ። ጊዜያቱም አንዳንድ ጊዜ ለ 12 ሰዓታት ያህል ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ ለ72 ሰዓታትም የሚጾም ጾም ነበር አስቴ . 4 . 16። ከዚህ በላይ የሆነው የጾም ሰዓት ግን በተአምራዊ እንጂ በሥጋዊ ኃይል እንደሆነ መገመት ያስቸግራል ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች እውነተኛ ና ልባዊ የሆነ የጾም ሥርዐት አይታይም ነበር ። ስለዚህም ነቢያት በኀብዝነት ይደረግ የነበረውን ጾም ተቃውመዋል ። ገሥጸዋልም ኢሳ. 58 ፡ 3 - 7። ኤር . 14 ፡ 12 ።

## በሐዲስ ኪዳን

መድኃኒታችን ክርስቶስ የፈሪሳውያንን ከንቱ ውዳሴ ነቀፈ እንጂ ጾምን አልተቃወመም ። ጾም የትሕትና ራስን ለእግዚአብሔር የማስገዛት ምልክት ስለሆነ በስውር እንጂ በዓዋጅ መሆን እንዳይገባው ጌታችን አስተማረ ። ማቴ 6 . 16 - 18 ።

በጌታችን ጊዜ የነበሩት አይሁድ በሳምንት ሁለት ቀናት ሰኞንና ሐሙስን ይጾሙ ነበር ሉቃ 18 ፡ 12 የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርትም አብዝተው ይጾሙ እንደነበር በማቴዎስ ወንጌል 9፡ 14 - 17 ተገልጦአል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ ማቴ 4 ፡ 2 ። ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ እርሱ በነበረበት ዘመን በየዓመቱ ይህን ጾም እንዲጾሙ አላዘዛቸውም እንዲያውም ደቀ መዛሙርቱ ለምን እንደማይጾሙ ተጠይቆ የሚከተለውን መልስ ሰጠ ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሠርገኞች ሊጾሙ አይችሉም ። ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ በሚለይበት ጊዜ ይጾማሉ ። ማር 2 ፡ 18 - 22

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በማለቱ ሐዋርያት የፈሪሳውያንን ጾም አይነት እንዳይጾሙ መከልከሉን ያስረዳል። ሙሽራው በሚለይበት ጊዜ እንደሚጾሙ ይህም በሐዋርያት ዘመን





www.ethiopianorthodox.org

የጌታ የሞቱ መታሰቢያ ሆኖ በየዓመቱ ለሁለት ቀናት ይጾሙ ነበር ። ዛሬም የአክፍሎት ጾም እየተባለ በየዓመቱ ይጾማል።

በሐዋርያት ዘመን ስለ ጾም ቀዋሚ ሕግ አልነበረም ስለዚህም እስከ ሁለተኛው መቶ ዓመት ጾም የግል ፈቃድ ነበር ምእመናኑ አብዝተው ሆነ አሳንሰው ለመጾም ነፃነት ነበራቸው ።

ሐዋርያትም መዓረገ ክሕህነትን ከመቀበል በፊት ጾም እንደሚገባ በተግባር አሳይተዋል ።

ለምሳሌ ጳውሎስና ባርናባስ በመንፈስ ቅዱስ ተጠርተው ሥልጣነ ክህነትን ከመቀበላቸው በፊት ጾመዋል ። ግን ለምን ያህል ቀን እንደ ጾሙ አልተገለጠም ። የሐዋ . 13 :2 ። 14 ፡ 23

በመሠረቱ የሐዲስ ኪዳን ጾም ስለ ክርስቶስ ፍቅር የተደነገገ ነው ። በየሳምንቱ የሚጾሙት ዐርብና ረቡዕ ክርስቶስ በፍቅሩ ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ ለማስታወስ ነው ። ዐርብ ጌታችን ኢየሱስ የሞተበትበሞቱም ድኅነተ ዓለም የተፈጸመበት ስለሆነ ይጾማል ረቡዕም እንዲሰቀልና እንዲሞት የተወሰነበት በመሆኑ እንዲጾም በሐዋርያት ተደንጎአል ። ዲስቅ . 7፡ 4

ከዚህም ሌላ በጥንት ጊዜ ክርስቲያኖች አንድ አይነት ፈተና ሲገጥማቸው ምህላና ጸሎት ይዘው ለተወሰኑ ቀናት ይጾሙ ነበር ። እንደዚሁም ንስሐ ሲገቡ ካህኑ በፈቀደላቸው መሠረት ይጾሙ እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ዛሬም ይህ አይነት ጾም ይሠራበታል ።

ከጥምቀትና ከቁርባን በፊት ሰውነትን ለማንጻት ማንኛውም ክርስቲያን መጾም እንደሚገባው ሐዋርያት አስተምረዋል በኋላም በአራተኛው ምእት ዓመት በትልቁ ባስልዮስና በዮሐንስ አፈወርቅ ዘመን ከቁርባን በፊት ጾም ተሠርቷል ።

ከዚህም የተነሣ ከታላላቅ በዓላት በፊት በዋዜማው ስለ በዓሉና ስለ ቅዱስ ቁርባን ክብር መጾም ተጀመረ ። ይልቁንም ከትንሣኤ በፊት ለአንድ ሳምንት ያህል በየዓመቱ እንዲጾሙም የታወጀው በዚሁ በአራተኛው ምእት ዓመት ነው ። ዩዛም ሳምንት ቅዱስ ሳምንት ወይም ስሙነ ሕማማት እየተባለ ይጠራ ጀመረ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 40 ቀንና 40 ሌሊት የጾመው ጾም በአራተኛው ምእት ዓመት እንዲጾም ተወሰነ ነገር ግን እንደዛሬው ለሰባት ሳምንታት ሳይሆን ለሁለት አንዳንዴም ለሶስት ሳምንታት ብቻ ይጾም ነበር ።

ከመጀመሪያው ምእት ዓመት እስከ ሶስተኛው ዘመን ድረስ በጾም ቀን ዳቦ ውሃና ጨው ይፈቀድ ነበር ። በኋላ ግን ፍራፍሬና አታክልት ይበላ ጀመር ። እየቆዩም አንዳንዶቹ ዕንቁላልና ቅቤ ውየወጣ ለት ወተት ይጠቀሙ እንደነበር ይነገራል ። ዛሬ ግን ዕንቁላልና ጥሉላት አልኮል ነክ መጠጥም እንዲወስዱ ቤተ ክርስቲያን አትፈቅድም ።

ለማጠቃለል ያህል በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት የጾም ጥቅም መንፈሳውያን ነገሮችን ለማሳወቅና ሕይወትን ለማደስ ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ከዝሙትና ከሥጋዊ ደስታ ርቆ በመጾም በመመጽወትና በመጸለይ እግዚአብሔርን ያገለግላል ጾም ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ያገናኛል ። ሕይወትን ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ ያደርሳል ። ጾም ሥጋን ለነፍስ ያስገዛል ። ከኃጢአትና ከስህተት በመከልከል የሚሆን ጾም ሕወትን ወደ እውነተኛ መንገድ ይመራል።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

# ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፯ የዞረ

ለሀገራቸው ሲሞቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ በኢትዮጵያ የሚዘነመውን መከራ ተስቅተውና እግሬ አውጭኝ ብለው ወደ አገራቸው ሸሽተው በመሄዳቸው ተደም ብለው በእስክንድርያው ፓትርያርክ ጵጵስና ተሾመው የነበሩት አቡነ አብርሃም የሊቀ ጵጵስና ውን ስፍራ ወስደው ከቆዩ በኋላ በሞት ስለተለዩ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ ።

ነፃነታችን ሲመለስ ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ወደ መንበረ ጵጵስናቸው እንዲመለሱ ቢጠይቁ አንደኛ የኢትዮጵያ መነኮሳት ሊቀ ጵጵስናውንም ሆነ ፓትርያርክነቱን እንዳይሾሙ የሚከለክል ሕግ አለመኖሩ ሁለተኛ በመከራ ጊዜ ሸሽቶ በሰላም ጊዜ ወደ ሹመት ልመለስ የሚለው አሳብ ተገቢ አለመሆኑ መሠረት ሆኖ በኮፕትና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ሰፊ ክርክር ይካሄድ ጀመር ።

የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ከላይ የተገለጹት መሠረታውያን ክርክሮች ስለ አስቆጡአቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በወረራው ጊዜ ግንኙነቱ ተቋርጦ በምርጫ የሾመቻቸው ጳጳሳትና ሊቀ ጳጳስ በሥልጣናቸው እንዳይሠሩበት የውግዘት ቃላቸውን አስተላለፉ ።

በዚህም ጊዜ አቡነ ዮሐንስ ከሊቀ ጵጵስና መንበራቸው ወርደው አዲስ አበባ በቅዱስ ሩራኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ እያስተማሩ እንዲቀመጡ ተደረገና የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ክርክር ቀጥሎ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ በደረጃ ሙሉ መብቷን አገኘች።

አቡነ ዮሐንስም ወደ ቀደመው ንቡረ ዕድነት ሥራቸው ቢመለሱ በማስተማር ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋጽኦ ሰፊ መሆኑ ተገምግሞ የአዲስ ዓለም ንቡረ እድ ሆነው እንዲያስተምሩና በዚያው በደብሩ እንዲቀመጡ ተደረገ ።

አቡነ ዮሐንስ በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን በንቡረዕድነቱ መዓርግ ላይ ሆነው ጉባኤያቸውን አስፍተው በማስተማር ላይ ሳሉ በተወለዱ በ73 ዓመት ዕድሜያቸው ሰኔ 3 ቀን 1948 ዓ.ም. አርፈው በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጸመ ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

« ሁሉን ፈትኑ የሚሻለውንም መርጣችሁ ያዙ »

(1ኛተሰ ፡ 5 ፡ 21)

''ስሕተት እንኳን ቢሆን የማናውቀው ነገር ሊኖር አይገባም'' ይል ነበር ይባላል ክልደተ ክርስቶስ በፊት የነበረ ክርስቲያን በሚል የቅጽል ስም የሚጠራው ፈላስፋ ሶቅራጦስ ፡ ሐዋርያ ጳውሎስም በዚሁ አንፃር ''ሁሉን ነገር ፈትኑ ። መልካም የሆነውንና የሚሻለውንም መርጣችሁ ያዙ'' አለ ።

ከፍ ብሎ በተገለጠውም መሠረት አራት ዓይነት የድርሰት መንገዶች ማመልከታችን ይታወሳል ። ይሁን እንጂ የእያንዳንዱን የድርሰት ዓይነት ጥቅምና ጉዳት ወይም ደካማና ብርቱ ይዘቱን ሳንገመግም አጥንት ጉልጥምቱን አጋብስን ለመዋጥ አንገደድም ። ይኸውም የመምረጥና የማሻሻል ዕድል አለን ማለት ነው ።

ለምሳሌ በቁጥር 1 ስለውበት ማንፀባረቂያ መከሥተ ውበት ስለተሠኘው የድርሰት መንገድ ስናወሳ ያልጠቆምነው ሌላ ነገር አለ ። ይኸውም የውበት ተቃራኒ አስመስለን የምናየውን የመጥፎነትን ሁኔታ አልጠቀስንም ፡ ታዲያ መጥፎ ብለን የምንገምተው ከሌለ ውብ ብለን የምንጠራውም ነገር መኖር አይችልም ። ሁለቱ ተቃራኒ ነገሮች በተነፃፃሪነት መቅረብ አለባቸው ።

ለማስረጃ ያህል መልካም ሥራ ወዳድ የሆነ ገበሬ ደኑን መንጥሮ መሬቱን አርሶ አፈሩን አንቀርቅቦ በማለስለስ ያለማውን የአዝርዕትና አትክልት ዓይነት ፍራፍሬ የመላበትንና በአበቦች ያጌጠ ለም መሬት ወይም የጓሮ አትክልት ስናይ ውበቱ ሊማርከን ይችል ይሆናል ። በአንፃሩ ደግሞ ጫካ ሆኖ ቁጥቋጦ (እሾህ አሜኬላው) ወርሶት ምንም ዓይነት አዝርዕትና አትክልት ሳይበቅሉበት የእንስሳትና አራዊት መፈንጫ የአዕዋፍ ማፊጫ የሆነ መሬት ስናይ ምንም ዓይነት ውበት ስለሌለው ጠፍ መሬት አድርገን እንመለከተዋለን ። ነገር ግን በመሠረቱ የመሬቱ ተፈጥሮ ከዚያ ከለማው መሬት ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ጠፍ መሬት ብለን የምንጠራው የልማድ አነጋገር እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም ። ባለሙያ ገበሬ ቢይዘው ኖሮ የተለየ ውበት ሊኖረው ይችል ነበርና ነው ። እንግዲያውስ ውበት የሥራ ውጤት መሆኑ ነው ።

ወይም አንዱ ጥሩ ምግብና ልብስ አግኝቶ በማጌጥ ሲያምርበት ሌላው ምግብና ልብስ አጥቶ በተጐሳቆለ ኑሮ ላይ ቢታይ ወይም ታማሚ ቢሆን ዕኩል መሳ ለመሳየሆነ ውበት አይታይባቸውም እንል ይሆናል ። ታዲያ በተፈጥሮ ትክለ ሰውነት ወይም በአካል አንድ ዓይነትን ቅርፅና መልክ ወይም ተመሳሳይ ሰብአዊ አቋም ያላቸውን ሰዎች በአጋጣሚ የኑሮ ደረጃ መዘበራረቅ ጉዳይ ከፍና ዝቅ ቢያደርጋቸውም አንዱን አይተን ውብ ሌላውን ለይተን መልከ ጥፉ በማለት ማንጓለል አይገባም ።

እንግዲያውስ ውበት የአስተያየትና የሰብአዊ ግምት ጉዳይ እንጂ ሌላ ትርጉም አይኖረውም የሚል ፍልስፍናዊ ግምገማ አለ ። ይህም ዓይነቱ ትንታኔ ከድርሰት ጥበብ ጋር አብሮ የሚጓዝ በመሆኑ ሼክስፔር ሲናገር ''ጥሩ ወይም መጥፎ ተብሎ የሚጠራ ምንም ነገር የለም ፤ ይህን አስተሳሰብ የፈጠረ የሰዎች አስተያየት ነው'' አለ እንግዲያውስ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ መልካም ነው ''እነሆ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ » ተብሎ ተጽፎዋል ። ዘፍጥ .1 ሐዋርያ ጳውሎስም ''እግዚአብሔር ከፈጠረው ነገር ሁሉ ወዳቂ የሚሆን ምንም ነገር የለም'' ሲል ጽፎአል ። እንግዲያውስ የሰውም መልካምነትና መጥፎነት የሚለካው በጠባይና በሥነ ምግባሩ ወይም ባጠቃላይ በሃይማኖቱ ጽናት እንጂ በአፍአዊ መልኩ አይደለም ።

ይህም ከሆነ እንኳንስ በመልክና በጠባይ በኅብረ ሥነ ምግባር ሞራሉ የወደቀ (ወይም በደኅነት ኑሮ የተጎሣቆለ ፣) ወይም ጤና ያጣ ወገናችን ቢኖር በሀብትና ጤንነት ከትምህርት ጋር አገናኝቶ በልቶ ጠጥቶ ለብሶም በማጌጥ እንዲያምርበትና ከሞራል ውድቀትም እንዲነሣና አዲስ ሕይወት የሚያገኝበትን መንፈሳዊ ምክር እንዲያገኝ ማድረግ ሲገባ አንገዋሎ በመጣል ከኃጢአት በሞት (በኖሉት) ጠባቂዎች ላይ ፍርድን እንደሚያስከትል ተጽፎአል ።

በተራ ቁጥር 2 የሰብአዊ ርኅራኄን ስሜት ይፈጥራሉ ተብለው የሚታሰቡትም ከእኛ ሥልጣንና ቁጥጥር ሥር ሆነው የሚያስደስቱንና የሚያሳዝኑን ወይም የምንወዳቸውና የምናፈቅራቸው ፍጥረታውያን ነገሮች ብቻ ሊሆኑ አይገባም ከምንወዳቸውና ከምናፈቅራቸው ጐን የምንጠላቸውና የምንፀየፋቸው ፍጥረቶች አሉ ። እንግዲያውስ በፍቅር ከሚማርኩን ነገሮች ይልቅ ለምንጠላቸውና ለምንጸየፋቸው ታናናሽ ፍጥረቶችም የተለየ አድናቆትና የማፍቀር ስሜት ወይም ሰብአዊ ርኅራኄ እንዲኖረን ያስፈልጋል ማለት ነው ።

ለምሳሌም ለርግብ ጫጭቶች ሕይወት የምንራራውን ያህል የዕንቁራሪትም ሕይወት በከንቱ ሲጠፋ የምናሳየው ስሜት የጭካኔ ምልክት ነው ።

ከሰው ዘርም ወገን እንኳ በሥልጣን ዕድገትና በኃይል ሥራ አመራርን የማይቀይሱ ይኖራሉ እንበል ታዲያ ደራሲ (ጸሐፊ) የሰው ፊት አይቶ ሳያዳላ የበኩሉን ምክር ለመለገሥ ለሁሉም በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ ፍትሕ ርትዕ እንዲሠፍን የሚያደርግ ጽሑፍ በማቅረብ ፈንታ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# በኤሉባቦር ክፍለ ሀገር በጋምቤላ አውራጃ የሚገኙ ብሔረሰቦች

የኢሉባቦር ክፍለ ሀገር በተፈጥሮ ልምላሜ የታወቀ ክፍለ ሀገር ነው ። ክፍለ ሀገሩ እንደሚጎራበቱት እንደ ከፋና ሲዳሞ ሰፊ የቡና ምርት የሚገኝበት በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በጉመሮ የሻይ ሰብል የታወቀ ሆኖአል ። ከክፍለ ሀገሩ ተራሮችና ኮረብቶች ጥግ አያሌ ወንዞች ይፈልቃሉ ። በተለይም የሶር ፏፏቴ እንደጢስ አባይ ተመልካቹን በትዝታ የሚስብ ኃይል አለው ። በኢሉባቦር ደን ውስጥ ከዝሆን እስከ ሚዳቋ በያይነቱ የዱር አራዊትና አእዋፍ ይገኛሉ ።

የኢሉባቦር ክፍለ ሀገር እንደሌሎቹ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች መኖሪያ ነው ። እነዚህ ብሔረሰቦች በቋንቋቸው በቤት አሠራራቸው በሙዚቃቸውና በዕለታዊ የኑሮ ሁኔታዎች የተሰበጣጠረ የባህል ቅርስ እንዳላቸው ይታወቃል ።

በዚህ እትም ላይ በተለይም በጋምቤላ አውራጃ ስለሚገኙ ብሔረሰቦች እንመለከታለን ። በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ከሚገኙ አውራጃዎች መሃል ጋምቤላ አንደኛው ሲሆን ቀድሞ ዳር ሀገር ከሚባሉት ሥፍራዎች እንዲያውም ራቅ ያለው ነበር። አልፎ አልፎ የጋምቤላ መኖር ይሰማ የነበረው በአውሬ አዳኞች በኩል ነገር ። በተረፈ አልፎ አልፎ በደጋው የነበረ የመኪና መንገድና ሌላው የመገናኛ ዘዴ ያልደረሰው ቢቀና በሣምንት በሚገኝ የአውሮፕላን ጉዞ የሚደረስ አውራጃነበር። ይህ አውራጃ በሁለንተና መነጠል በብሔረሰቦችም ከፍተኛ ተጽእኖ በማስከተል የመሻሻልን ጭላንጭል ሳያዩ እስከ አብዮታችን ፍንዳታ ቆይቶአል ።

በአውራጃው ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች መሃል ነባርነት ያላቸው የአኝዋክ ፣ የኑዌር የመዣንገር የኮምና የአፑዋክ ብሔረሰቦች ይገኙባቸዋል ። የእነዚህ ብሔረሰቦች ባህል የተመሳሰለ ልዩነትም ያለው ነው ።

## ጋብቻ

በብሔረሰቦቹ ዘንድ አስቀድሞ መፋቀር ኋላም ደንቡና ሥርዐቱ በሚያዘው መሠረት በሠርግና በጥሎሽ መጋባት የነበረ ነው ። ለምሳሌ ያህል የኑዌር ብሔረሰብ የጥንት ማጫ የቀንድ ከብቶች ጥሎሽ ነበር ያም አግቢው በቤተዘመድና በሽማግሎች አማካይነት ለምትታጨው ልጃገረድ ቤተሰብ ሰባት ማለፊያ የቀንድ ከብቶች መርጦ ይልካል ። ይህ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በድጋሚ 18 ምርጥ የቀንድ ከብቶችን ይልካል የተላኩትን የቀንድ ከብቶች የልጂቱ አባት እናትና የቅርብ ቤተዘመድ በየራስ ቆጥሮ ይከፋፈላቸዋል ። የሠርጉ ዕለት ሲቃረብ ማንኛውም ይዘጋጅና ልጅትዋ ትዳራለች ። ባለፈው ሥርዐት ሙሽራይቱና ሙሽራው ታጅበው መንገድ ከጀመሩ በኋላ ሙሽራው ሙሽሪቷን እየተንጠራራ መግረፉ አልበቃው ብሎ ቤት ከደረሰም በኋላ ሕግዋን ለመግሰስ በሚደረገው ትንቅንቅ በሰውነትዋ ላይ የመደብደብ ጉዳት ያደርስባት እንደነበረ ሁሉ በዚህም ብሔረሰብ ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ከገባ የወንድ በላይነቱን ለማሳየት ከፍ ዝቅ አድርጎ ይደበድባት ነበር ።

በዚህ ሁኔታ የሚጠለደው የመጀመሪያው ልጅ የሚያድገው በልጂትዋ አባትና እናት ቤት ነው ። እርስዋ ወደ ወላጅችዋ ቤት ትሄድና እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ትቆያለች ። ከሁለት ዓመት በኋላ ባል ሚስቱን መልሶ የሚያገኘው በወላጅችዋ ፈቃድ ነው ከዚህ ውጪ ቢፈጽም ካሣ ይከፍላል ወይንም ሚስቱን መልሶ አያገኝም ። ሌላው በአንድ ብሔረሰብ ውስጥ ሁለት ጎሣዎች በነፍስ ግድያ ደም ቢቃቡ በሁለት ወጣቶች መሃል ጋብቻ አይደግፍም ።

በአኝዋክ ብሔረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ ያለው በሚመጣለት ጥሎሽ ሲከብር ቆይቷል ። በዚህ ብሔረሰብ ዘንድ ወንዱ ለሴትዋ የሚሰጠው ማጫ በብሔረሰቡ አጠራር ድሙይ የተባለው የጨሌ ጌጥ ነው ። ይህ የጨሌ ጌጥ ብዛቱ እስከ አምስት የሚደርስ በዋጋም እያንዳንዱ መቶ ሃያ ብር የሚደርስ ነው ። እንግዲህ ሚስት ለማግኘት ስድስት መቶ ብር የሚያወጡ ድሙዩዎች ሊኖሩት ይገባል ማለት ነው። ይህ ብቻ አይደለም በዚሁ ብሔረሰብ በአንዳንድ ጎሣዎች ዘንድ ጥሎሽ በጦሮች በአንገት ድሪዎችና በአምባሮች ሳቢያ ይከፈላል ። እነዚህን የመሳሰሉትን የጥሎሽ መተኪያዎች ያላገኘ ጎበዝ ቆንጆዋን ባይኑ ብቻ ሲያማትር ይቀራል እንጂ የማግባቱ ነገር ዘበት ነበር። ሌላው የዚህ ማካካሻ ጋብቻ የሚሻው ወጣት የደረሰች እህት ካለችው ለፈለጋት ልጃገረድ ወንድም ለውጥ ሰጥቶ ጋብቻውን ይፈጽማል። በነገራችን ላይ በጋምቤላ አውራጃ የሚገኙ ብሔረሰቦች እቃዎችን በጨሌ በማጌጥ ፡ በቅል ላይ የልዩ ልዩ እንስሳትን ቅርጽ የሚያሳዩ ምስሎችን በመንቀስ ከአክርማ የቤት ውስጥ ጌጦችን በመሥራት የሰጎን እንቁላል በልዩ ውበት በመሸለም ፡ ከዝሆን ጥርስ በክንድ የሚጠለቅ አምባር በመሥራት የታወቁ ብልሆች ናቸው ስለሆነም ለጋብቻ የሚውሉትንም አብዛኛዎቹን ጌጦች የሚሰሩዋቸው ራሳቸው ናቸው ።

እንደተመለከትነው ሁሉ ጋብቻው በብዙ ወጪ ይፈጸማል ። ወጣቶቹ ከተጋቡ በኋላ የፍቺው ጉዳይ የጠበቀ ነው። ለመለያየት የሁለቱ ሃሳብ በሀገር ሽማግሌዎች ተሰምቶ ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል ። ያለዚያ አባወራው ሚስቱን አስወጥቶ ሲያባርራት በጎሣዎች መሃል ከፍተኛ ግጭትና የከብት መዘራረፍን ሁኔታ ያስከትል ነበር ።

ኃዘንን በሚመለከት ፣ በብሔረሰቦች ዘንድ ሰው ሲሞት ኃዘን ይበረታል ። ይህም በሌሎችም ክፍላተ ሀገር ብሔረሰቦች ዘንድ የቆየ ኋላ ቀር ባህል ነው ።

ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል



# ልማት በቤተ ክርስቲያን


## ሸምብጥ ቅዱስ ሚካኤል

በጎጃም ሀገረ ስብከት በባሕር ዳር አውራጃ በጣና ሐይቅ አጠገብ በሚገኘው በሸምብጥ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም የእርሻ ልማት ተቋቁሞ አጥጋቢ ውጤት እያስገኘ ነው ።

በዚሁ በሸምብጥ ቅ ሚካኤል አካባቢ ድአ መምሪያ በተገኘ የተራድኦ ገንዘብ በተቋቋመው የካህናት ማሰልጠኛ የሚሰለጥኑ ካህናትም በተግባረ ዕድ የልማት ሥራዎችን ያካሒዳሉ ።

ስለአጠቃላይ ሁኔታው የማሰልጠኛውን ርእሰ መምህር መሪጌታ ዘለዓለም የተቋቋመው ልማት በማን አማካይነት ተቋቋመ ? የሚካሔደውና የሚመራውስ በእነማን ነው ? ልማቱ የሚካሔደውስ በምን ኃይል ነው?

መልስ በሸምብጥ ቅ/ ሚካኤል ገዳም የተቋቋመው ልማት በሀገረ ስብከቱ ሊ



ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በልማቱ ሥራ ላይ ተገኝተው ካህናቱን ሲያበረታቱና ሠርተው ሲያሳዩ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራ ደስታን አነጋግረናል ።

ጥያቄ ፣ በሸምብጥ ቅዱስ ሚካኤል ገዳ

ቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አማካይነት ነው ። የሚካሄደው በገዳሙ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

በሚያገለግሉ መነኮሳት ሲሆን ሥራውን የሚያከናውኑ ካህናት በፈረቃ ተመድበው በየፈረቃ ቸው የልማቱን ሥራም ሆነ የቤተ ክርስቲያን አገልልግሎት ያ

ለተባለው ልማቱ የሚካሔደው በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በዕርዳታ በተገኘው የውሃ መሳቢያ ሞተር ነው ። ይህ ሞተር በጣም ትልቅ በመሆኑ የጣናን ሐይቅ

ጥያቄ እርሻ ስንል በብዙ ዓይነት ይከፋፈላል እስከ አሁን የተሠራውን የተክል ዓይነት ቢገልጹልን ?

መልስ እስከአሁን ከተሠሩት የእርሻ





ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የውሃ ግጠሚውን ሞተር ይዘው ተክሉን በማጠጣት ላይ እንዳሉ

ከናውናሉ ።የሚመራውም በገዳሙ አስተዳዳሪ በመምህር ተክለ ሕይወት ማኅሀንቱ ነው ።

ልማቱ የሚካሄደው በምን ኃይል ነው?

ውሃ ያለ ችግር እየሳበ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ነው ።

ጥያቄ የተቋቋመው ልማት ምንድንነው?

መልስ የተቋቋመው ልማት እርሻ ነው

አትክልት ዓይነቶች በቆሎ ቀይና ነጭ ሽንኩርት ፡ ቆስጣና ፡ሰላጣ ፡ ጥቅል ጎ

ወይ. ገጽ ጽ ዞርል



# ትምህርተ ግዕዝ

# የግእዝ ትምህርት

## ትምህርት 4

| | |
|---|---|
| አብ | አባት |
| አበው | አባቶች |
| እኁ | ወንድም |
| አኃው | ወንድሞች |
| ሐም | አማት ( ወንድ ) |
| ሐማን | አማቶች |
| አፍ | አፍ |

መከራት ፡ ከዚህ በላይ የተጻፉት ቃላት በዕርባታ ዝርዝር ሲረቡ ሳድስ የነበረው መድረሻቸው ወዳካዕብነት ይለወጣል በ3ኛ መደብ ግን « ሁ » የሚል ሌላ ፊደል ይጨምራሉ አሁን እንዴት እንደሚረቡ እንመልከት ።

**ነጠላ**

| | |
|---|---|
| አቡየ | አባቴ |
| አቡከ | አባትህ |
| አቡኪ | አባትሽ |
| አቡሁ | አባቱ |
| አቡሃ | አባትዋ |

**ብዙ**

| | | |
|---|---|---|
| አቡነ | | አባታችን |
| አቡክሙ | ተባ | አባታችሁ |
| አቡክን | አን | » |
| አቡሆሙ | ተባ | አባታቸው |
| አቡሆን | አን | » |

አሁንደግሞ በረፍተ ነገር ለመሥራት እንድንችል የሚከተሉትን ቃላት እናጥና።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀሎ | አለ | ኀበ | ወደ |
| ሖረ | ሔደ | ውስተ | በ - ውስጥ |
| ትዕይንት | ከተማ | እወ | አዎ |
| ጻኅን | ደሕና | አኮ | አይደለም |
| ኑ | ቃለ ተስእሎ | እ. | አሉታ |

### በረፍተ ነገር

ጻሕንኑ ውእቱ አረጋዊ አቡከ
እወ ጻሕን ውእቱ አቡየ
አይቴ ሀሎ አቡክሙ
ሀሎ አቡነ ውስተ ቤት
አይቴ ሖረ አቡክን
ሖረ አቡነ ኀበ ትዕይንት
ሀሎ አቡሁ ውስተ ቤት
ኢሀሎ አቡሃ ውስተ ቤት
ዝንቱ ውእቱ አቡሆሙ
አኮ ዝንቱ አቡሆሙ
ዮሐንስኑ ውእቱ አቡሆን
አኮ ዮሐንስ አቡሆን

ሽማግሌው አባትህ ደህና ነው ?
አዎ አባቴ ደህና ነው
አባታችሁ የት አለ ?
አባታችን በቤት ውስጥ አለ
አባታችሁ የት ሄደ ?
አባታችን ወደ ከተማ ሄደ
አባቱ በቤት ውስጥ አለ
አባትዋ በቤት ውስጥ የለም
አባታቸው ይህ ነው
ይህ አባታቸው አይደለም
አባታቸው ዮሐንስ ነው?
አባታቸው ዮሐንስ አይደለም

ምልማድ መልመጃ

«እኁ ሐም አፍ » የሚሉትን ቃላት « አብ » የሚለውን ቃል በአረባችሁበት የዕርባታ መንገድ ለማርባት ሞክሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

## በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ...

ከገጽ ፲ የዞረ

በነዚህ ብሔረሰቦች ዘንድም በተለይም የቤተሰቡ ርእስ የሆነ አባት ወይም እና ት ሲሞቱ ቤተዘመዱ ራሱን እስከመጉዳት ይደርሳል ኃዘንተኞቹ ለተወሰነ ጊዜ እህል ውሃ አይቀምሱም ። ለሦስት ወር የዘፈን ነገር አይነሳም ፤ ሴቶች ጌጣጌጣቸውን አያደርጉም ። ይህ ከአርባ ቀን እስከ ሦስት ወር ሊራዘም ይችላል ። ሟቹ በህይወቱ ሳለ ያፈራው ሀብት ለልጆቹ ይሰጣል ።

የጋምቤላ አውራጃ ብሔረሰቦች እንደ ሌሎቹ ወንድሞቻቸው ሁሉ የአብዮትን ፍሬ ተካፋዮች እንደመሆናቸው ሁሉ የምርትና የባህል ዘመቻው ሂደት የነበረው ኋላ ቀር ልምድ እንዲወገድ ከፍ ያለ ሚና እየተጫወተ ነው ። ለምሳሌም ያህል ቀድሞ በጥሎሽ እጦት የጋብቻ ጉዳይ አስቸጋሪ ሆኖ ቢቆይም ዛሬ ሁሉ ቱ ወጣቶች ከተፈቃቀዱ ጋብቻው ይፈጸማል። በትንንሽ ምክንያቶች በብሔረሰቦች መሃል ይካሄድ የነበረ ግጭትና የከብት ዝርፊያ ዛሬ ቀርቶ ሁሉም በሰላም በወንድማማችነት ልማትና የመሠረተ ትምህርትን በመሳተፍ ላይ ናቸው ባለፈው አጉል ልምድና እምነት ግንባርን ሰውነትን በስለት መብጣት የተለመደና ቅርጽን ያበላሽ የነበረ ድርጊት በተሰጠው ንቃተ ህሊናና ትምህርት ቀርቷል ።

ለምለሙ የጋምቤላ አውራጃ ዛሬ አውራ ጎዳናዎች የተከፈቱለት ስለሆነና አውራጃው ለልማት ሥራ የታጨ በመሆኑ ሰፊ የተስፋ ውጋጋን ይታይበታል ።

በተለይም በኢትዮጵያ ወንዞች ላይ ከተዘረጉት ድልድዮች ሁሉ የላቀ ድልድይ በባሮ ወንዝ ላይ መዘርጋቱ ለጋምቤላ አውራጃ ብሔረሰቦች ከፍተኛ ደስታን ያስከተለ ከመሆኑም በላይ የወደፊት አለኝታቸውን አጠንክሮላቸዋል ።




## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት...

ከገጽ ፭ የዞረ

እንዲሁም የሊቦን ፤ የደብረ ታቦርን የጋይንትን አውራጃዎች በይፋ ጎብኝተዋል በሊቦ አውራጃ አዲስ ዘመን ከተማ ሲደርሱ የአውራጃው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች የከተማውና የአካባቢው ሕዝብና ካህናት ደማቅ የሆነ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።


ከዚያም የሊቦ አውራጃን ጉብኝት ፈጽመው ወረታ ሕፃናት ማሳደጊያ መ ት ቤት ሲደርሱ የደብረ ታቦር አውራ



ሊቃውንተ ጎንደር ለቅዱስነታቸው በየተራ ቅኔ ሲያበረክቱ



የጎንደር ክፍለ ሀገር ረዳት ዋ / አስተዳዳሪ ጓድ ዘመነ ካሣ ቅዱስነታቸውን እንኳን ደህና መጡ በማለት ንግግር ሲያደርጉ ።



ካህናተ ጎንደር በዝማሬ ላይ እንዳሉ

ጃ ረዳት አስተዳዳሪ ቀኝዝማች አሻግሬ መራ አቶ ፀጋዬ በርሄ የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ዋና ፀሐፊ ፊታውራሪ አጥናፉ አየ በጎንደር የሚገኙ የሕጻናት አስተዳደግ ት ቤቶች ሊቀመንበር የከተማው ሕዝብ ካህናቱ መምህራኑ ና ተማሪዎቹ በሰልፍ ተቀብለዋቸዋል ። እንዲሁም ወጣት ተማሪዎቹ ግጥሞችንና ቅኔዎችን አበርክተዋል ። ከዚያም ጉዞ ወደደብረ ታቦር ከተማ ሆኖ በደብረ ታቦር ከተማ አብዮት አደባ

ወደ ገጽ ፲፯ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# ሊቀ ማእምራን ሐዋዝ

ሊቀ ማዕምራን ሐዋዝ ጥሩነህ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጎንደር አውራጃ መካነ ነገሥታት ግምጃ ቤት ማርያም በተባለችው ጥንታዊትና ታሪካዊት ደብር በ 1884 ዓ.ም ከአባታቸው ከመምህር ጥሩነህ አስረሳኸኝና ከእናታቸው ከወ ሮ ጥሩነሽ ባይነሳኝ ተወለዱ ከዚያም በጊዜው ታዋቂ ከነበሩት የጎንደር ሊቃውንት ከአለቃ ዮሐንስ ፣ ከመምህር ተክለማርያም ፣ ከመምህር ገብረኢየሱስና ከመምህር ዘአማኑኤል ዘንድ ጾመ ድጓ ፣ ድጓ ቅዳሴ ፣ ቅኔ ትርጓሜ ሐዲሳትና ብሉያት ተምረዋል ።



በመካነ ነገሥታት ግምጃ ቤት ማርያም በዲቁና ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በጊዜው መኪና ስላልነበረ በእግር ከ15 ቀናት በላይ ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ ተጉዘው ቅስና ተቀብለው ተመልሰዋል ።

በጠላት ወረራ ጊዜ የግምጃ ቤት ታቦተ ማርያም እንዳትቃጠል ከአባታቸው ጋር በመሆን አውጥተው በማሸሸ ከቃጠሎው እንድትድን አድርገዋል ። ከዚያም በተወለዱበትና በተማሩበት ሥፍራ በመወሰን በተክሊል ካገቧቸው ባለቤታቸው ወ ሮ ያመነሽ ተበጀ 12 ልጆችን አፍርተዋል » የጋብቻ ዘመናቸውም እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ 65 ዓመት ነበር። ሊቀ መዕምራን ሐዋዝ ጥሩነህ አባታቸው ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ የግምጃ ቤት ማርያምን አስተዳዳሪነት በመረከብ የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎት እስከ ዕለተ ሞታቸው ሲመሩ ቆይተዋል። በነበራቸው መንፈሳዊ አባትነት በሕዝብ ዘንድ « ጻድቁ አባታችን » የሚል ቅጽል ስም አውጥቶላቸው ነበር ቤተ ክርስቲያንዋም ከጊዜብዛት የተነሳስላረጀች ምዕመናንን በማስተባበርና መዋጮም በማሰባሰብ በዘመናዊ መልክእንድትታደስ አድርገዋል ። በትጋትና በቅንነት ደብሯን ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ለጥቂት ቀናት ታመው ሣለ ቤተሰቦቻቸው ወደ አዲስ አበባ ሄደው ከፍተኛ ህክምና እንዲታከሙ ጠየቋቸው እሳቸው ግን እመ ብርሃን በራእይ ጊዜ ሞትህ ደርሷል ብላ የገለጸችልኝ ስለሆነ የእኔ መሄድ ከንቱ ድካም ነው አሉ ። ቤተሰቡም በጣም ስላስቸገራቸው በግድ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደረገ ፣ ሆኖም እሳቸው ቀድም ሲል እንደገለጹት ሐምሌ 16 ቀን 73 ዓ.ም የኪዳነ ምሀረት ዕለት በግልጽ እርሳቸውን ሊጠይቁ በቆሙ ወዳጆቻቸውና ቤተ ዘመዶቻቸው ፊት ግብረ ዘወሀበ ከኒ ፈጸምኩ በማለትና ለእርሳቸው ብቻ በሥውር የሚታዩአቸውን « ኑ ግቡ እንግዶቼ ናችሁ እረ ግቡ በኋቸው በሩ ላይ የቆሙት ትልልቅ እንግዶቼ ናቸው » በማለት ከተነጋገሩ በኋላ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች አስከሬናቸውም ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲሄድ ተደረገ ።

የሊቁ እረፍት እንደተሰማም ሊቃውንተ ጎንደር በግምጃቤት ማርያም ደብር ተሰባስበው የቤተ ክርስቲያኑ ደወል ተደውሎ ቀሳውስት ሰዓታት መዘምራኑ ማኅሌት ቆሙ ፣ ሊቃውንት በሙሉ በተገኙበት ሙሉ የአደራረስ ሥርዓተ ፍትሃት ሲደርስላቸው ካደረ በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴው በማግሥቱ ተፈጽሞ ወተቀበልዎ መላእክት በስብሐት ወአብእዎ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር በመስማት አስከሬናቸው ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ካህናትና መዘምራን እየታጀበ ወደተዘጋጀለት መካነ መቃብር ተጉዞ ሊቃውንት ምእመናን ወዳጆና ዘመድም በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት…

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ባይ የአውራጃው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ባለሥልጣኖች የከተማውና የአካባቢው ሕዝብ ሊቃውንት መዘምራንና ካህናት በሰልፍ ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

የአውራጃው ሪ/ዋና አስተዳዳሪ ቀኛዝማች አሻግሬ መራ እንኳን ደህና መጡ በማለት ንግግር ያደረጉ ሲሆን እንዲሁም በፕሮግራሙ ቅደም ተከተል ሕዝቡን ፣ ካህናቱን በመወከል የተለያዩ ሰዎች ንግግር አድርገዋል ።

እንዲሁም የተመደቡ ሊቃውንት ቅኔ አበርክተዋል ። ከዚያም ለሁለት ቀናት ያህል በደብረ ታቦር ከተማ ውስጥ እየተዘዋወሩ ጥንታውያን ገዳማትን ቀጥሎም የጋይንት አውራጃን ጐብኝተዋል ከደብረ ታቦር ከተማ ተነስተው ጋይንት ርዕሰ ከተማ ነፋስ መውጫ ሲደርሱ የአውራጃው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ባለሥልጣኖች በአውራጃው የሚገኙ ሊቃውንት የከተማውና የአካባቢው ሕዝብ በሰልፍ ሆነው ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል። በዚያም በፕሮግራሙ ቅደም ተከተል መሠረት የአውራጃውን ሕዝብ በመወከል የተለያዩ ሰዎች ንግግር ያደረጉ ሲሆን የተመደቡ ሊቃውንትም ቅኔ አበርክተዋል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴን በጎበኙ በት ወቅት

የደብረ ታቦር አውራጃ የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ት/ቤትን ፣ ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳትን ጐብኝተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ከጋይንት ጉብኝት መልስ በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ የሚገኙ ጥንታውያን ገዳማትን የጐበኙ ሲሆን በተለይ በእስቴ ጥንታዊውን ደብረ ሃይ


ወረዳ ሕዝብ በወረዳው የሚገኙ ሊቃውንት ካህናት መዘምራን በሰልፍ ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። በዚሁ ጊዜ የተለያዩ ሰዎች ንግግር ያደረጉ ሲሆን የተመደቡት ሊቃውንትም ቅኔ አ

ባበል አድርጐላቸዋል ።

## ጐጃም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተመሳሳይ ሁኔታ የጐጃምን ክፍለ ሀገር ለመጐብኘት ኅዳር 7 ቀን 1974 ዓ.ም. ከቀኑ 9 ሰ ዓት ላይ ባህር ዳር ከተማ ሲገቡ ደማቅ አቀባበል ተደርጐላቸዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን ሌሎችንም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ከሺ.ሜ ማርያም ተነስተው በአንበሳሜ በኩል ሲያልፉ የአንበሳሜ ከተማ ሕዝብ እጅግ ደማቅ የሆነ አቀባበል አድርጐላቸዋል ።

ከዚያም ባህር ዳር ከተማ ከመድረሳቸው በፊት ጓድ ኃይሌ መለሰ የባህር



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገነት ተራራ ላይ ሆነው የጎንደርን ከተማ ሲመለከቱ

ማኖት መካነ ኢየሱስን ጐብኝተዋል ። በዚሁ ቦታ የደብሩ አስተዳዳሪ የሆኑትን አሊቃ ዓለማየሁ ካሣ መልአከ ገነት ብ

በርከተዋል ። ከእስቴ ጉብኝት በኋላ በፋርጣ ወረዳ የምትገኘውን ጥንታዊት የሆነችውን ማኅደረ ማርያምን ጐብ



በወረታ የሕፃናት ማሳደጊያ ት/ቤት ተማሪዎቹ ቅዱስነታቸውን በያሬዳዊ ዝማሬ ሲቀበሉ ።



የት/ቤቱ ሕፃናት ለቅዱስነታቸው ዕቅፍ አበባ ሲያበረክቱ

ለው ሲሰይሟቸው የመጻሕፍት ሐዲሳት መምህር አባ ኃይለ ሚካኤል መጋቤ ሐዲስ ተብለው ተሰይመዋል ።

እንዲሁም በእስቴ ከተማ በተደረገው አቀባበል የእስቴ ወረዳ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ኃላፊዎች የእስቴ

ኝተዋል ። በዚሁ ቦታ ሲደርሱ የአካባቢው ሕዝብና ሊቃውንት እጅግ ደማቅ የሆነ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ቀጥሎም መካነ ሰማዕት ገላውዴዎስን ሺ.ሜ ማርያምን ሌሎችንም አድባራት ሲጐበኙ ሕዝቡ በየስፍራው ደማቅ አቀ

ዳር አውራጃ አስተዳዳሪ የአውራጃውን ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅት ባለሥልጣኖችን አስከትለው ከከተማው ወጥተው አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚያም የጐጃም ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪ



ያጅ ሊቀ ሥዩማን ያዕቆብ ጌታሁን እንኳን ደህና መጡ በማለት ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል ፣ እንዲሁም ሌሎች የተመደቡ ሰዎች በየተራ ንግግር አድርገዋል ።

የተመደቡ ሊቃውንትም በየተራ ቅኔ አበርክተዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩና ተከታዮቻቸው በባህር ዳር አው

ላቸዋል ።

ከዚህም በቀር በነዚሁ ገዳማት የሚገኙ ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳትን ጐብኝተዋል ። ቀጥሎም የአገው ምድር አውራጃን የቆላ ደጋ ዳሞትን የመተከል አውራጃዎችን እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል። በሶስቱም አውራጃዎች ርዕሰ ከተማዎች የየአውራጃው መንግሥታዊ

ወንዶቹ እንደበሬ እንሸጥና እንለወጥ ነበር ። አሁን ግን ሰብእናችን ተከብሮ እንደሰው ለመቆጠር በቅተናል አሁንም እንደሌሎች ወንድሞቻችን የሃይማኖት ነፃነት በማግኘታችን ከቅዱስነትዎ ፊት ቀርበን ችግራችንን ለመግለጽ ስለቻልን ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል ብለዋል ” በዚሁ ወቅት ብሔረ



ቅዱስነታቸው በጐጃም ክፍለ ሀገር የብር ሸለቆን እርሻ ልማት ሲጎበኙ

ራጃ የሚገኙ የልማትና ልዩ ልዩ ድርጅቶችን እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል ።

ከነዚህም የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፣ የባህር ዳር ፣ አውራጃ አ . ኢ ወማ.አ.አ..ሴማ መ.አ..ገ.ማ. የመምህራን ማኅበርን የአርበኞች ማኅበር ጽ ቤቶችን እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል ።

እንዲሁም በጣና ደሴቶች የሚገኙ ጥንታውያን ገዳማትን ማለትም ዳጋ እስጢፋኖስን ናርጋ ሥላሴን ዑራ ኪዳነ ምህረትን እየተዘዋወሩ በመጐብኘት በነዚህ ጥንታውያን ገዳማት ለሚኖሩ መናንያን እና ለአካባቢው ነዋሪዎች አገልግሎት የሚውሉ ወፍጮዎች እንደሚተ ክሉላቸው ቅዱስነታቸው ቃል ገብተው

ና ሕዝባዊ ድርጅቶች ተጠሪዎች የየከተማው ነዋሪ ሕዝቦች በሰልፍና በጭብጨባ ሊቃውንቱና መዘምራኑ በዝማሬ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። በተለይ በመተከል አውራጃ በጓንጓ ወረዳ ሰርካይስ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር የሚኖሩ የሻንቅላ ብሔረሰቦች ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ክዳኑን ማስጨረስ ባለመቻላቸው ለክዳኑ የሚሆን ቆርቆሮ እንዲፈቀድላቸው ለቅዱስነታቸው አመልክተው ቅዱስነታቸውም ቆርቆሮው የሚበቃቸውን ያህል ተገዝቶ እንዲሰጣቸው ስለፈቀዱ የብሔረሰቦቹ ተወካይ በብሔረሰቦቹ ስም ደስታቸውን በመግለጽ ባደረጉት ንግግር “ቀድሞ ሴቶቹ እንደላም

ሰቦቹ በባህላቸው መሣሪያ የሻንቅላ ብሔረ ሰብ ጨዋታ አሰምተዋል ። ከዚህ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ባሰሙት ንግግር «ሁኔታውን በሁለት መንገድ እንመለከተዋለን። 1ኛው በሀዘን 2ኛውን በደስታ ። በሀዘን ስንል በሥላሴ አርአያ የተፈጠሩ ወገኖቻችን እንደእንስሳ ሲሸጡና ሲለወጡ ማየት እጅግ የሚያሳዝን በመሆኑ ። በሌላ በኩል በደስታ ነው ለተባለውም እናንተ ከዚያ ሁሉ መከራ ተላቃችሁ ተገፎ የነበረው ሰብአዊ መብታችሁ ተከብሮ የሃይማኖት ነፃነታች



www.ethiopianorthodox.org

ሁንም አውቃችሁ እንደሊሎቹ ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ በአንድነት ስለተቀብ

ተክለ ሃይማኖት በሁለቱም ክፍላተ ሀገር የሚያደርጉት ጉብኝት ፈጽመ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሙተከል አውራጃ በጓንጓ ወረዳ የሚኖሩትን የሻንቅላ ብሔረሰቦች ባነጋገሩበት ወቅት

ላችሁንና ቤተ ክርስቲያንም ሠርታችሁ እምነታችሁን ለማክበር በመቻላችሁ ነው ብለዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ

ው በሄዱበት አኳኋን ኅዳር 17 ቀን 1974 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብተዋል ።

ተስፋ ጥሩነህ ።

## ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከገጽ ፲፪ የዞረ

መንና አባጀሽኝ ጎመን ፣ በርበሬና ቲማቲም ፣ ቀይስርና ካሮት ፣ ዱባና ፋሮ ፣ በተለይ አንዱ ፍሬ ከ2 ኪሎ በላይ የሚመዝን ስኳር ድንችና የመሳሰሉት ለምተዋል ። ከተጠቀሱት ሌላ በተጨማሪ በመልማት ላይ የሚገኙ አሉ ፣ እነሱም ሙዝ ብርቱካን ኮክ ፣መንደሪን፣ማንጎ ፣ፓፓዬ ሸንኮራና ቡና የመሳሰሉት እየለሙና በቅርብ ጊዜ ፍሬ እንደሚሰጡ እየተጠበቀ ነው ።

ከነዚህ ሌላ ምን አይነት ልማት ተጀምሮአል ?

መልስ የልማቱ እቅስቃሴ እንዲጠናከር ባለው የአጭርና የረጅም ጊዜ ፕላን የእህል ዓይነቶችን ለመዝራት ሰፊ እርሻ ተጀምሮአል በመሠረተ አሳቡም ጤፍና ጥራጥሬ ተዘርተዋል ፣ በአበቃቀላቸውና አሁንም እንደምናያቸው በሰብል አያያዛቸው ጥሩ ውጤት ይገኛል ተብሎ ተስፋ ተጥሎባቸዋል ።

ጥያቄ ለዚህ የእርሻ መሣሪያ ያሻል ለዚህ እቅድ ገንዘብ ከየት ተገኘ ?

መልስ ፦ ቀደም ሲል በሸምብጥ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም ከተጀመረው ልማት በተገኘው ገንዘብ በሮች ሊገዙ ችለዋል መሣሪያዎቹም በዚሁ ዓይነት ተገዝተዋል።

ጥያቄ በባሕር ዳር ከተማ የካህናት ማሰልጠኛ በልማት ረገድ ምን ይሠራል?

መልስ ማሰልጠኛው የጎንደርና የጎጃም ን ሀ / ስብከቶች ካህናት የሚያሰለጥን ሲሆን እነዚህ ካህናት በማሰልጠኛው ከሚሰጣቸው የቀለም ትምህርት ሌላ ዕደ ጥበባትን እንዲማሩ ይደረጋል ፣

በዚህ ዕቅድ መሠረት ካህናቱ ኮርሱን እስኪጨርሱ ድረስ ልዩ ልዩ ሥራዎችን በመሥራት የገንዘብ ገቢ ምንጮች ሊፈጥሩ ችለዋል ።

ጥያቄ እስከአሁን በማሰልጠኛው በተግባረ ዕድ በኩል ምን ተሠርቷል ?



በባሕር ዳር የካህናት ማሠልጠኛ የማሠልጠኛው ርእስ መምህር መ ዘላ ለም ደስታና የልማቱ ኃላፊ መምህረ ሕይወት ግዛውነቱ በልማቱ ቦታ እንዳሉ

መልስ መንበር ፣ መስቀል ፣ ቁም ሳጥን ጠረጴዛ ወምበሮችና ትንንሽ የቤት ዕቃዎች ተሠርተው የሚገዙትን ሰዎች በዋጋ ሳያስቸግር ለመሸጥ ተችሎአል ።

ጥያቄ ትምህርት ቤቱ ከተከፈተ እስከ አሁን ድረስ ስንት ካህናት ሰልጥነዋል?

መልስ በማሰልጠኛው እስከአሁን ድረስ 225 ካህናት ሰልጥነዋል ።

ላቀረብልንዎ ጥያቄ መልስ ሰጥተውናል በአጠቃላይ የሚሰጡን አስተያየት ካለ፣

በአጠቃላይ የምሰጠው አስተያየት ቢኖር የልማት እንቅስቃሴዎችን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በጎጃም ሀገረ ስብከት እንደተጀመረው ልማት በየሀገረ ስብከቱ እንደ አመችነቱ ቢጀመር ለቤተ ክርስቲያናችን ሕልውና ጠቃሚ ይሆናል ።

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ርዳታ ባይለየን ልማቱ በበለጠ እንደሚጠናከርም አንጠራጠርም ።

በየገዳማቱና አድባራቱ ካህናት በብዛት እንደመኖራቸው በዚያ ልክ ዳቦ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው ። ይህ መሆኑ ከታወቀ ካህናቱ ወደ ልማት ተሠማርተው ገቢ በማስገኘት ከችግር እንዲላቀቁ ቢደረግ ደህና ነው ።

በየካህናት ማሰልጠኛዎች የሚሰለጥኑ ካህናት ከቀለም ትምህርት ሌላ በዕደ ጥበብ ሥራ እንዲሰለጥኑ የበለጠ ቢታሰብበት የሰለጠኑትም ካህናት ወደመጡበት ሲመለሱ በሙያቸው እንዲሰማሩ የሚያበቃ መመሪያ ቢወጣ ሥራችን አጭዶ መበተን አይሆንም ።

ካህናቱ እንዲበቁና በቤተ ክርስቲያናችን የልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ በየካህናቱ ማሰልጠኛ ቢደረግ የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና አመራር የበለጠ የሚያስደስት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ ።

ከዚሁ ሌላ በቃል የተናገርነውን ሁሉ ተጨባጭ ለማድረግ የልማት ሥራው ይዘትና ሒደት በሥዕላዊ መግለጫ ቢዘጋጅ ጠቃሚ ስለሚሆን በሸምብጥ ቅ ሚካኤል የተጀመረውን ልማት የሚሠሩትን መነኮሳት በሥራ ላይ እንዳሉ መጐብኘት መልካም መስሎ ይታየኛል በማለት መሪጌታ ዘለዓለም ደስታ አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

አዎ በመጽሐፍ ቅዱስ « በውሃ ሁሉ አጠገብ የምትዘሩ ብፁዓን ናችሁ » እንደሚለው ሁሉ የሸምብጥ ልማት የተቋመው በኢትዮጵያ አሉ ከሚባሉት ሐይቆች አንዱ በሆነው በጣና ሐይቅ አጠገብ ስለሆነ የተጀመሩት የልማት ሥራዎች አጥጋቢ አይደሉምስለሆነም ጅምሩ መልካም ስለሆነ ይህ የልማት እንቅስቃሴ በይበልጥ ቢጠናከር ለመላዋ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም እንደሚሆን ይገመታል ።

በለጠ አበበ



www.ethiopianorthodox.org

# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

ከገጽ ፱ የዞረ

አድርጎ የሚመለከትበት ዓይን ካለው አድላዊ ከመሆን አይዘልም ።

በተራ ቁጥር 3 የተመለከተውም ኮሜዲ የተሠኘው የድርሰት መንገድ የሰውን ዘር ሁሉ በምድራዊ ተድላ ደስታ ማዕበል የሚያሰጥም አስቂኝና ቧልት (ኩምክና) የሞላበት ድርሰት ብቻ ማመንጨት በኅብረተሰብ ሞራል ላይ አንድ ዓይነት ያልተጠበቀ የሞራል ውድቀት ማስከተል ይሆናል ።

ለማስረጃ ያህል የጥንት ሮማውያንን የጀግንነትና የጦረኛነት ታሪክ ስንመለከትና ዘግየት ብሎ ከደረሰባቸው የወኔ መቀዝቀዝ ጋር ማነፃፀሩ ይበቃል ። ኤውሮፓን ፣ መካከለኛውን ምሥራቅና ሰሜን አፍሪቃንም ሁሉ በቁጥጥራቸው ሥር ከአደረጉ በኋላ ያ ሁሉ ኃይላቸው ተንኰታኩቶ ወድቆ በሥልጣኔ ዕድገት እነርሱ ከደረሱበት ደረጃ ባልደረሰ ሕዝብ ወረራ ቁጥጥር ሥር የዋሉት ከቅንጦት ኑሮ ብዛት እንደነበር ተጽፎአል የነርሱም ቅንጦት ክርስቲያኖችንም ጭምር እንኳ አሰጥምዋቸው ነበር ማለት ይቻላል ። ስለዚህም ቀድሞ በዘመነ ሰማዕታት ወደፊት ይገሠግሥ የነበረው የቤተ ክርስቲያን እርምጃ በከፊል እስከ መገታት ደርሶ ቅንጦትና ዘበናይነት ተስፋፍቶ በነገረ መለኮት ጥናት ጠጉር ስንጠቃ ውስጥ የገቡበት ዘመን እንደ ነበር ተጽፎአል ። ከዚህም የተነሣ በአንዲት ሃይማኖት ላይ ልዩ ልዩ የመናፍቅነት ትምህርት በማፍለቅ የክርክር ሸንጎ መከፈት ግዴታ ሆኖ ነበር ።

በሌላም በኩል የቦታ ርቀት ባስከተለው መከፋፈል ምክንያት የሥልጣን መበላለጥ ተፈጥሮ አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ይቃጣው የነበረው ውድድር ከዚሁ ከቅንጦት ኑሮ የመነጨ ሆኖ የወንጌል ስብከትን መስፋፋት ወደኋላ መግታት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ዘግይተው ለተነሡ እምነቶች መግቢያ ቀዳዳ ትቶላቸው ተገኝተዋል ።

ይህም የአጉል ቅንጦት ኑሮ ካስከተላቸው ጠንቆች አንዱ ሰውን ከአራዊት ጋር ከማታገል ትርኢት አድርሰዋል ። በተለይም ሳይሠሩ የመክበርና ያለምንም በቂ አገልግሎት በዘበናይነት የሌሎችን እጅ አይቶ የመኖር ልምድ ከክርስቲያናዊ ሥርዓተ ኑሮ ጋር አብሮ የሚጓዝ ባለመሆኑ ሁልጊዜ ቧልትና አስቂኝ የሆኑ ነገሮችን ብቻ መፈለግ የክርስቲያን ደራሲ ዓይነተኛ ዓላማ አይደለም ።

ስለዚህም የኮሜዲ ድርሰት ተፈላጊነቱ ገደብ ሳያልፍ በመጠኑ አእምሮን ለማደስና ጥቂት ለማዝናናት ያህል ብቻ እንጂ "የሞኝ ዘፈን ሁል ጊዜ ሙኒት ሙኒት" እንደተባለው መሆን የለበትም ። ማርም እንኳ ቢሆን ሲበዛ መምረሩ አይቀርምና ነው ።

ቆስ መክብብ አጥናው



# « ጉቦ የዓይናማዎችን ሰዎች ዓይን ያሳውራል »

ጉቦ በግዕዝ ቋንቋ ሕልያን ይባላል።ሕልያን ማለትም ማስወንጀያ ማሳሳቻ ፣ ማታለያ ፣ መደለያ እንደማለት ነው ፣ ጉቦ የሚፈጸመው በገንዘብ ብቻ አይደለም በዘመድ በወዳጅ በእምቻ በጋብቻ በጉልበት አገልግሎት ቃልን አለዝቦ ከንቱ ውዳሴን በማቅረብ ሊፈጸም ይችላል ።

ጉቦ ከማንኛውም ሰው በማነኛውም መንገድ መፈጸም እንደማይገባው ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው ይናገራሉ ኦሪ ዘዳ 16፥ 18 - 20 « አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ በሀገርህ ደጅ ሁሉ በየነገዶችህ ፈራጆችንና አለቆችን ሹም ፤ ለሕዝቡም ቅን ፍርድን ይፍረዱ ፣ የሰው ፊትም አይተህ አታድላ ጉቦ የጥበበኞችን ዓይን ያሳውራልና የጻድቅንም ቃል ያጣምልና ጉቦ አትቀበል በሕይወትም ትኖር ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔርም የሚሰጥህን ምድር ትወርስ ዘንድ እውነተኛውን ፍርድ ተከተል» ይላል ።

በጉቦ ምክንያት ብዙ ሰዎች ከመዓርጋቸው ወርደዋል ከክብራቸውም ወድቀዋል በጉቦ ምክንያት ከተጎዱትና ከተዋረዱትም ሰዎች ጥቂቶችን ለትምህርት ያህል ቀጥለን እንመልከታቸው በለዓም የሚባል አንድ ሰው ነበር እርሱም ሀብተ መርገም የተሰጠው ስለሆነ ውሀውን ሲረግመው ይነጥፋል ዕንጨቱንም ሲረግመው ይደርቃል ሰውንም በረገመው ጊዜ ይጠፋ ነበር ይባላል በእርሱ ዘመን ባላቅ የሚባል የሞአብ ንጉሥ ነበር ከነገደ እሥራኤል ጋር ስምምነት አልነበረውም በጦርነት ተዋግቶ እንዳያጠፋቸው በውጊያ የማይችላቸው ሆነ ስለዚህ ብዙ ገንዘብ እስያ ዘናረግሞ እንዲያጠፋለት መልእክተኞችን ወደበለዓም ላከ በለዓም ከባላቅ የተላከለትን ጉቦ ተቀብሎ እስራኤልን ረግሞ ለማጥፋት በአህያው ላይ ተቀመጠና ጉዞውን ቀጠለ ።

መልአከ እግዚአብሔር ሰይፉን መዝዞ ከመንገድ ላይ ጠበቀው መልአኩም ለመጀመሪያ ጊዜ ለአህያይቱ ተገልጾ እንዳታልፍ ከለከላት ለአህያይቱ የታየው መልአክ ለበለዓም ስላልታየው ያንን በታ ተራምዳ እንድታልፍ መላልሶ በዱላ ዠለጣት እንደ ሰው አፍ አውጥታ በጉቦ ተደልሎ እስራኤልን ረግሞ ለማጥፋት የሚጓዘውን በለዓምን ዘልፋዋለች በመጨረሻም ለአሕያይቱ የተገለጸው መልአክ እግዚአብሔር ለበዓልም ተገልጾ ጉቦ የተቀበለበትን ርግማን እንዳይ ረግም ከለከለው በርግማኑም ፈንታ «ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምስራኤል»ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል ኃጢአትም ከእስራኤል ይወገዳል ብሎ ተናግሯል ዘጸ 22፥ 21 -36

ይህንንም መሠረት በማድረግ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲናገር « የቅን መንገድንትተው ተሳሳቱ የባሦርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ እርሱ የዓመጻን ደመወዝ ጉቦን ወደደ ፡ ነገር ግንስለመተላለፉ ተዘለፈ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ ብሏል 2ኛ ጴጥ . 2 ፡ 15

በዘመነ ኦሪት ካህናት መንፈሳዊውን አስተዳደር ይዘው በእግዚአብሔር ስም የሚያምኑትን አማንያንን ያስተዳድሩ ነበር ለምሳሌ በሙሴ ጊዜ ታላቅ ወንድሙ አሮን መንፈሳዊውን አስተዳደር ይዞ ይመራ እንደነበር እንዲሁም ኤሊ በዘመኑ በሊቀካህናትነትመንፈሳውያን ሕዝቦችን በሚገባ ያስተዳደር ነበር ።

ለእርሱም አፍኒን ፤ ፊንሐስ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት እርሱ እየደከመ ሲሄድ ልጆቹ ተተክተው ሕዝቡን በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩል ያገለግሉ ጀመር ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ቅኖች አገልጋዮች ሆነው አልተገኙም በጣም ጉቦኞችና አስነዋሪ ተግባርን የሚፈጽሙ ስለሆኑ ሕዝቦቹን በከፉ ሥራቸው አስመረሩአቸው ሕዝቡም ወደ ኤሊ እየሄዱ አባት እንደመሆኑ መጠን እንዲመክር ላቸው ይነግሩት ነበር ኤሊም ልጆቹን ከጉቦኝነታቸውና ከሌላም መጥፎ አድራጎታቸው እንዲታረሙ ይመክራቸው ነበር እነርሱ ግን የአባታቸውን ምክር ሰምተው ከጉቦኝነታቸው አልተከለከሉም ።

እግዚአብሔር በሚፈጽሙት የተንኮል ተግባር ተቀይሞ በአካባቢያቸው የሚኖሩትን ኢሎፍላውያን በጠላትነት አሥነሳባቸው እስራኤላውያን ጠላት በተነሡባቸው ጊዜ ሕዝቡ የጦር መሣሪያቸውን አዘጋጅተው ሲነሡ አፍኒንና ፊንሐስም ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከሕዝቡ ጋር አብረው ዘመቱ ።

ከሁለቱም ወገን ጦርነት ተጀምሮ ውጊያው ሲፋፋም አፍኒንና ፊንሐስ በጦርነቱ ላይ ወደቁ ታቦተ ጽዮንም ተማረከች በጦርነት ከተሰለፉት እስራኤልም አብዛኞቹ በጦርነቱ ላይ ሲያልቁ የቀሩት ተማረኩ እንዲሁም አውጭኝ እግሬ እያሉ በሩጫ ያመለጡም ይገኛሉ ከጦር ሜዳ ያመለጠ አንድ ሰው ወደ ኤሊ ሂዶ የአፍኒንና ፊንሐስን መሞት የታቦተ ጽዮንን መማረክ ስለነገረው በድንጋጤ ከተቀመጠበት ወንበር ወድቆ ሕይወት ሥጋው አለፈ 1ኛ ሳሙኤል 4 ፡ 1 - ፍ. ም ።

የሰውን ገንዘብ ያለ አገባብ በጉቦ መልክ የሚነጥቁ ሰዎች ሁሉ የሚጠፉት ብቻቸውን አይደለም ሌላውንም ከጉዳት ከመጣል አይመለሱም ። ክቡር ዳዊት የሰው ልጆች በዚህ ዓለም ቢፈጽሚቸው የሚጠቀሙባቸውንና የሚጎዱባቸውን ሲናገር « አቤቱ በድንኳንህ ማን ያድራል በተቀደሰው ተራራህስ ማን ይኖራል ይልናላቀረበው ጥያቄ ራሱመልስ ሲሰጥ « በቅንነት የሚሄድ እውነትን የሚያደርግ በልቡም እውነትን የሚናገር ዘመዶቹንም የማያስድብ ለባልንጀራው ምሎ የማይከዳ ጉቦን የማይቀበል ለዘለዓለም አይታወክም » ብሏል መዝ 14 ፡ 1 -5 ።

ነቢዩ ኢሳይያስ በጉቦና በልዩ ልዩ ጥቅም ዓይነ ልቡናቸው ተጋርዶ እውነትን ከመሥራት የተለዩትን ሰዎች ሲመከ



www.ethiopianorthodox.org

ር « ወደዚህ ሕዝብ ሂድና መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉም ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱም በዓይናቸው እንዳያዩ በጆሮአቸው እንዳይሰሙ በልባቸው እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአል ጆሮአቸውም ደንቁሯል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል በላቸው አለኝ ይላል ኢሳ 6 ፡ 10 ይኸው ነቢይ በተጨማሪ ሲናገር « ክፉ ማድረግን ተው መልካም ትሠሩ ዘንድ ተማሩ እውነትን ፈልጉ ክፉውን ወደቅንነት መልሱ ለድኃ አደጉም ፍረዱ አለቆች አመጸኞች ሌቦችን ተከታዮች ሆኑ ሁሉ ጉቦን ይወዳሉ ዋጋን ለማግኘት ይሮጣሉ ። ወላጆች ለሌሏቸው አይፈርዱም » ብሏል ኢሳ 1 . 16 .23

ጉቦም ሆነ ሌላ አስነዋሪ ተግባር ሊፈጸም የሚችለው የእውነት ምልክት ከሰው ልቡና ፈጽሞ በተፋቀ ጊዜ ነው እውነትን ከሰአብአዊ ተፈጥሯቸው ፈጽመው ለመፋቅ አንዳንድ ሰዎች ጉቦንና የመሳሰሉትን አስነዋሪ ተግባሮች ያዘወትራሉ ።

በጉቦና በግል ጥቅም ዓይነ ልቡናው የታወረ እውነትን አያስተውልም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሚያስምርበት ወቅት መዓርጋችን ምጡቅ አእምሮአችን ረቂቅ የሚሉ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ነበሩ ይሁን እንጂ ዓይነ ልቡናቸው በጉቦና በልዩ ልዩ ጥቅም ስለታወረ እውነቱን በሐሰት ከመለወጥ በስተቀር ሌላ ቁም ነገር አይታይባቸውም ነበር ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ክርስቶስ ከእናቱ ማኅፀን ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ፈወ ሰው ይህም ፈውስ ፈሪሳውያን አላስደሰታቸውም ነገሩ ስላስደነቃቸውና ጥቅማቸውም ወደፊት እንደሚያቋርጥባቸው ተገንዝበው የተፈወሰውን ሰውና ወላጆቹን መልሰው መላልሰው ጠየቋቸው አዳኙ ክርስቶስ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ጉዳዩን በጥብቅ መከታተል ጀመሩ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራቱን በትምህርት ለመግለጽ የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ ብሎ ሲናገር ፈሪሳውያን ሰምተው ዕውራን የምትለን እኛን ነውን ቢሉት ክርስቶስ መልሶ ዕውሮችስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር የሥጋ እውርነት ለነፍስ አይተርፍምና አሁን ግን እናያለን ስትሉ አታዩምና በኀጢአት እንደ ተሸፈናችሁ ትሞታላችሁ በማለት የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ከእውነት የራቀ በጉቦና በተንኮል የተበከለ መሆኑን ግልጽ አድርጎ ነግሯቸዋል የዮሐን ወን 9 ፡40

ጉቦ የጥበበኞችን ዓይን እንደሚያሳውር ከመነሻው ላይ ተጠቅሷል ዓይኑ የማያይ ሰው ያለመሪ ለመሮጥ ቢሞክር ተደናቅፎ እንደሚወድቅና ጉዳትም እንደሚደርስበት ሁላችንም እናውቃለን በጉቦ ተደልሎ የሚሠሩትም ሥራ እንደዚሁ ነው አደናቅፎ ከድንገተኛ አደጋ ላይ ይጥላል ።

ጉቦ ለሰጭውም ሆነ ለተቀባዩ ሕገወጥ ድርጊት መሆኑን ሁሉም ሰው ተገንዝቦ ከአድራጎቱ መገታት አለበት ፣ ነገር ግን የተሰበረበት ነገሩ እንዲጠገንለትና ውሸቱ እንደ እውነት ሆኖ አሸናፊነትን እንዲያገኝ የጉቦ መደለያን ያቀርባል ሌላው ደግሞ ችሎታ ሳይኖረው ከሥራው ጋር ግንኙነት እንደሌለው በልቡ ሳይጠፋው ቦታው ከፍተኛ ደመወዝን ያስገኛል በሚለው መንፈስ በመመራት ብቻ ቦታውን ለማግኘት ሲል የገንዘብ የዘመዱ የወዳጁ የቃል ጉቦ ያለማቋረጥ ይጎርፋል ።

ባለሥልጣኑም በልዩ ልዩ መንገድ የቀረበለትን ጉቦ ከተቀበለ በኋላ ቢቻለው ጉዳዩን ከፍጻሜ ለማድረስ ይሞክራል ካልተቻለም ዴንታ አይኖረውም ጉቦ በልተሃልና ጉዳዩን መፈጸም አለብህ ተብሎ በዕዳ አይከሰስም ጉቦውን እንደበላው ይቀራል ጉቦ ሰጭውም ዓላማውንና ግቡን ባይመታለትም ከገንዘቡም ሆነ ከጉዳዩ ሳይሆን እንዲሁ በከንቱ ይቀራል ።

ስለዚህ የሚያዋጣው በእውነትና በትክክል መሥራትና ማሠራት እንጂ በጉቦ የተሸፈነ ሐሰት ስላልሆነ ማንኛውም ሰው ጉቦን ከማቀበልና ከመቀበል ተወግዶ በእውነትና በትክክል የመሥራት ፍላጎት እንዲያድርበት ያስፈልጋል ።ዓይንን በጉቦ ጨፍኖ ከመራመድ በእውነት መነጥር እየተመለከቱ መራመድ ይበልጣል ።

ቄስ ግሣነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ